


ጥንታዊትና ታሪካዊት ርእሰ አድባራት ወገዳማት አክሱም ጽዮን



በኢየሩሳሌም ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት
«ዴር ሡልጣን የኛ ነው »

ዋጋ ፪ ብር

# « ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ »



የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት



ጥምቀት

## « ሰላም በምድር »

« የጋዜጦችና መጽሔቶች———ለሰላም »

ቁጥር ፩ ጥር ፲፱፻፹፯ ዓ/ም

www.ethiopianorthodox.org

# « ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ »

ቍጥር ፩ ጥር ፲፱፻፹፯ ዓ/ም
አ/አበባ

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት፤ታሪክና ባሕል፣የመንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ዜና ለሕዝበ ክርስቲያን የሚያቀርብ» ስለሆነ «ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ» ተብሎ ተሠይሟል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ኮሚቴ እያተዘጋጀ በየወሩ አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

ስልክ 11 26 63
የመልእክት ሣጥን ቍጥር 1283
አዲስ አበባ
ጥር ፲ ቀን ፩ሺህ፱፻፷፯ ዓ/ም

## ማርእስት


| ተ.ቍ. | | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | ርእሰ አንቀጽ | ፪ |
| ፪ | የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ቃለ ምእዳን | ፭ |
| ፫ | ሰላም በምድር | ፯ |
| ፬ | እንደገና መወለድ | ፰ |
| ፭ | የመጀመሪያው ተአምር | ፲፪ |
| ፮ | ዝርወተ አጽሙ | ፲፬ |
| ፯ | አስተርእዮ | ፲፭ |
| ፰ | « ዶር ሡልጣን የእኛ ነው » | ፲፯ |
| ፱ | የጋዜጦችና መጽሔቶች መልእክት ለሰላም | ፲፰ |
| ፲ | ከሐሰተኞች መምህራን ተጠበቁ | ፳፫ |
| ፲፩ | የገና ትዝታ | ፳፭ |
| ፲፪ | የግሸን እመቤት | ፳፯ |
| ፲፫ | መልካም ምሳሌ | ፳፰ |
| ፲፬ | ጨዋታና ቁም ነገር | |


www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

# ሰላም ከሁሉም ለሁሉም

በሥነ ፍጥረት የተመላው ዓለም ከፍጡር ዕውቀትና ችሎታ በላይ በሆነ ጥበብና ጥንቃቄ የተዘጋጀ ነው ።

የፍጥረት አኗኗር ፥ እንቅስቃሴና ሂደት ሁሉ የተፈጥሮ ሕግና ሥርዓት አለው ። ሉተለያየ ተግባርና አገልግሎት የተዘጋጁ የምድርና የሰማይ ፍጥረታት ሁሉ የእንቅስቃሴ ሂደታቸውን ጠብቀው የሚኖሩበት መሥመር በአስደናቂ ጥበብ የተከናወነ ነው ። አንዱ በሌላው ተግባር ፥ ሌላው በሌላው ሀልወና ጣልቃ አይገባም ። የሁሉም ሂደት ድንበሩንና ወሰኑን ጠብቆ የሚኖር ነው ። ደረቅ ምድር የውቅያኖስን ፥ ወንዞች የባሕሮችን ፤ ፀሐይ የዝናምን ዝናም የጨለማን ፥ ሌሊት ፥ የቀንን ፥ ከዋክብት የእንስሳትን ፥ ዕፀዋት የጨረቃን የአገልግሎት ወሰን አይጋፉም ። እያንዳንዱ በየራሱ የየራሱን ተግባር ሥርዓቱን ጠብቆ ያከናውናል ። ሁሉም በየተወሰነላቸው አገልግሎት ይኖራሉ ።

ብዙ ጊዜ ሥርዓትና ሕግ ሲፈርስ ፥ ድንበርና ወሰን ሲጣስ የሚገኘው ከሰዎች ወገን ነው ። የሰው ኀሊና ሌት ከቀን ዕረፍት የሌለው በምኞት ክንፍ ሲበር ፥ ከሚያየው አልፎ በማያየው ዓለም ሲንሳፈፍ የሚኖር ኃይል ነው ። የምድሩ ተሰጥቶት የሰማዩን ፥ የሚመኝ ፥ ውሀውን ትቶ እሳቱን ፥ በረከቱን አልፎ መርገሙን ፥ ክብሩን አቃሎ ድኅነቱን ይመርጣል ። ስለሆነም የሰው ልጆች ሀልወና እምብዛም ከችግር ተላቆ አያውቅም ።

ችግሮች ዓለም ሲፈጠር አብረው የተፈጠሩ ፥ ወይም ወደ ሰው ሕይወት በግድ ለመግባት የኀሊናን በር የሚያንኳኩ አይደሉም ። በስነ ፍጥረት እንቅስቃሴ እግር ከእግር እንዲ ጊጋጭ ወይም እንቅፋትን እንደ ሚመስል ያለ አጋጣሚ ይኖራል ቢባልም ፥ ችግሮች አብዛኛውን ጊዜ የሚመነጩት ከራሳቸው ከሰዎች ምኞትና ግብር ነው ።

በስነ ፍጥረት መጽሐፍ የምናነበው ከእለተ እሑድ እስከ ዓርብ በየወገኑና በየዓይነቱ የተዘጋጁትን ፍጥረታት ሁሉ መልካም እንደሆኑ ተመልክቶ የስነ ፍጥረት ባለቤት ፈጣሬ ፍጥረት ጌታ እንደ ባረካቸው ነው ።

መርገሙም ሆነ ኃሣሩ ፥ ፍዳውም ሆነ ጥረት ግረቱ የመጣው በሰዎች ጥፋትና ስሕተት እንደሆነ ተጽፎአል ። ለምድርም ሾክና አሜከላ (እሾህና ኩርንችት) የማብቀል ሸካራ ጠባይ ያተረፈው ያው የሰው ድካምና የማስተዋል ጉድለት ነው ።

ዛሬም ዓለም እንደዱሮ ሲናተፍ ፥ በእሳትና ስለት ሲተላለቅ የሚኖረው ለሰላም በተፈጠረው ፥ ለሁሉም ሊበቃ በሚችለው ሠፊ ዓለም በጋራ ለመኖር የ ሚያስችለው የፍቅር ጥበብ ስለጎደለው ነው ።

የዓለም ጠበብት የምድርን በረከት ለሁሉ ማካፈልና ማጥገብ የሚችሉበትን ዕውቀትና ሙያ መፈልሰፍ በሚችሉበት አእምሮ የጥፋትና የእልቂት መሣሪያ በመፍጠራቸው የሰው ልጅ ዝርያውን ለማጥፋት በእሳት ኳስ ሲጫወት ይኖራል ። ዳቦ በተራበ ወገን መካከል የእሳት አሎሎ የሚወራወሩ ሞልተዋል ። ግን ሁሉም ለሁሉ ቢያስብ ፤ አንዱ የሌላውን መብትና ነፃነት እንደ ራሱ አድርጎ ቢመለከት ለጥላቻ ፥ ለጠብና አምባጓሮ ቦታና ጊዜ ሲኖራቸው ባልቻለ ነበር ።

የሰው ልጆች ኑሮ ፍቅርና መተሳሰብ ፥ መረዳዳትና ሁሉን መከፋፈል ያለበት እንዲሆን ፥ ለሱ ሊደረግለት የ ሚሻውን አንዱ ለሌላው እንዲያደርግለት የማስተማር ግዴታና ኃላፊነት ያለባት ቤተ ክርስቲያን የሰላም ድምጹዋን አሰምታ ትጮሃለች ። ቤተ ክርስቲያን ሰላምን እርቅን ፥ ፍቅርንና አንድነትን ከማስተማር የተለየ ዓላማና ጥሪ የላትም ። በማኅበረሰብ ሕይወት ከሥጋዊ አስተዳደር (መንግሥት) የምትጉዳኘው የማኅበረ ሰብን ሰላምና ደኅንነት በሚመለከተው መሥመር ብቻ ነው ። የጊዜያችን የፓለቲካና የሥነ ጽሑፍ ሰዎች በውል ሊገነዘቡት ያልቻሉት ታላቅ ነጥብ ቢኖር ይህ ብቻ ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ርእሰ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል ለመላው ሕዝበ ክርስቲያን ባስተላለፉት ቃለ ቡራኬ ፥

"ከእግዚአብሔር የተሰጠን የልጅነት ፀጋ ፍቅሩን እንድናውቅ ፥ የእውነትን መንገድ እንድንከተል ፥ የዘለዓለም ሕይወትና የክብሩ ወራሾች እንድንሆንየጥፋትንና የጨለማን ሥራ ሁሉ አስወግዶ ሰላምን መሠረተ ፥ ምን ጊዜም ቢሆን የእግዚአብሔር ሕጉ፥ትእዛዙ ፥ ምክሩና ቅዱስ ፈቃዱ ለፍጥረት ሰላምና ደኅንነት ስለሆነ የሰላም ወንጌልን እንማር" ብለዋል ።

እኛም በአዲሱ "ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ" መጽሔታችን "ሰላም ከሁሉ ለሁሉ" በማለት የእርቅ ፥ የሰላምና የብልጽግና ዘመን እንዲሆን መልካም ምኞታችንን እንገልጻለን ።

## ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ልደት ያስተላለፉት ቃለ ምእዳን

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ፤

የጠፋ በግ አዳምን ለመፈለግና ዓለምን ለማዳን በሥጋ የተገለጠው የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ልጆች ልትሆኑ ለተመረጣችሁ ፥ በእግዚ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ቃለ ምእዳን ሲያስተላልፉ

አብሔር ለተወደዳችሁና በቅድስናው ለተጠራችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ሁሉ የእግዚአብሔር ሰላምናጸጋ ይብዛላችሁ «እንኳን ለብርሃን ልደቱ በሰላም አደረሳችሁ»

"ሕፃን ተወልደ ለነ ወልድ ተውህበ ለነ
ሕፃን ተወለደልን ፥ ወንድ ልጅም ተሰጠን"
(ኢሳ ፥ ፱ ፥ ፮)

ይህ ቃል ዓለምን ለማዳን ይመጣ ዘንድ በእምነትና በተስፋ ይጠበቅ ለነበረው ለክርስቶስ የተነገረነው ።

"እነሆ ድንግል በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ትወልዳለች ስሙ አማኑኤል ይባላል ፥ አማኑኤል ማለትም እግዚአብሔር ከኛ ጋር ነው" ተብሎ የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ዘመኑ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር አንድና የሚወደውን ልጁን ወደ ዓለም ላከ እንደተጻፈውም ከንጽሕት ድንግል ማርያም ተወለደ ። ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው ሆነ ።

ከስነ ፍጥረት አስቀድሞ የነበረ ፤ በቃልነቱ ዓለምን የፈጠረ ፥ ሁሉ በርሱ የሆነ ፥ ከሆነው ሁሉ ያለርሱ ምንም ምን የሆነ የሌለ ቀዳማዊ ቃል (ቃለ እግዚአብሔር ወልድ) ሥጋ ሆነ በኛም አደረ ።

ዛሬ በዳዊት ከተማ በቤተ ልሔም የተወለደው ጌታ ለሰው ሁሉ የሚያበራ እውነተኛው የዓለም ብርሃን ነው ። ነቢያት የተነበዩለት ሐዋርያት የመሠከሩለት ፥ ሊቃውንትና መምሕራን ያስተማሩለት እውነተኛው የዓለም መድኃኒት ዛሬ ተወለደ ። በመወለዱ ብዙ ሰዎች ደስ ብሏቸዋል ።

የክርስቶስ ልደት በኃጢአት ጨለማ ተወርሶ የነበረውን ዓለም ወደ ብርሃን ለማውጣት ፥ ፈርሶ የነበረውን ድልድይ ለማደስ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካል ተቋርጦ የቆየውን ግንኙነት ለመቀጠል ጠፍቶ የነበረውን ሰላም ለመመለስና የፍቅርን መሠረት ለማጥበቅ ስለሆነ መላው የክርስቲያን ኅብረተሰብ በደስታና በምሥጋና ያከብረዋል ። ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ስለሰጣቸው የክርስቶስ ልደት ለክርስቲያኖች ሁሉ የዳግም ልደት ቀን ነው ። ሁላችን በሃይማኖት በጥምቀት ከእግዚአብሔር ተወልደናል ። የልጅነትን ክብር አግኝተናል ። የኃጢአት ሥርየት ተስፋ መንግሥተ ሰማያት ተሰጥቶናል ።

### የተወደዳችሁ ልጆቼ ፤

ለሁላችን ክርስቲያኖች የመዳን ቀን የሆነውን የክርስቶስን የልደት በዐል ስናከብር የተሰጠንን ሰላምና ያገኘነውን የልጅነት ክብር እያሰብን ሊሆን ይገባል። እኛ የኃጢአትን መንገድ በመከተል ለሕጉና ለትእዛዙ ያልተገዛን ጠላቶቹ ስንሆን የእግዚአብሔር ልጆች እንሆን ዘንድ ክብር እንደሰጠን ፥ ምን ያህል እንደወደደንም እናስተውል ፥ እሱ ንጹሕ በባሕርዩ ቅዱስ በአንደበቱም ሐሰት የሌለበት እውነተኛ እንደሆነ በርሱ ያመኑ ሁሉ ንጹሐን ቅዱሳን መሆን ይገባቸዋል ። በሥራው ፈጣሪውን የማይመስል ሁሉ ከእግዚአብሔር አልተወለደም ፥ እግዚአብሔርን አያየውም አያውቀውም ፥ አይወደውም፥እግዚአብሔር ጻድቅ ቅዱስ እንደሆነ ጽድቅን የሚሠራ ሁሉ እውነተኛ ነው ።

— ከእግዚአብሔር የተሰጠውን የልጅነት ጸጋ እንድንቀበል የጽድቅን መንገድ እንድንከተል የዘለዓለም ሕይወትና የክብር ወራሾችም እንድንሆን የእግዚአ



www.ethiopianorthodox.org

ብሔር የባሕርይ ልጅ ፣ በሥጋ ተገለጸ ፡— የጥልን ግድግዳ የጥፋትንና የጨለማን ሥራ ሁሉ አስወግዶ ሰላምን መሠረተ ።

ከእግዚአብሔር የተወለደ ከእግዚአብሔር የተማረ ኃጢአትን አይሠራም የእግዚአብሔር ልጅ ነውና ከእ ግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ አይበድልም በሕጉ በት እዛዙ ተመርቶ በምክሩ በትምህርቱ ጸንቶ ይኖራልና ፣ በክርስቶስ ክርስቲያን የተባለና በጥምቀት ከእግዚአብ ሔር በመወለድ የልጅነትን ክብር ያገኘ ሁሉ ወን ድሙን ይወዳል ። ወንድሙን የማይወድ ግን ከእ ግዚአብሔር የተወለደ የተማረ አይደለም ። በጥንት ስብከት የተነገረው ፣ በሐዲስ ኪዳን የተሰጠ አዲስ ትእዛዝ የርስ በርስ ፍቅር ነው ። የክርስቲያን መለ ያውና መታወቂያ ውም ሰላም ነው ። የሚያየውን ወንድሙን የሚጠላ የማያየውን ረቂቅ አምላክ እወ ዳለሁ ሊል እንደማይቻለው ተጽፎአል ። የእግዚ አብሔር ልጆችና የክፉ መንፈስ ተከታዮች ተለይ ተው የሚታወቁት በዚህ ነው ። ለወገኑ ሰላምና ፍቅር ያለው ሁሉ ከእግዚአብሔር መወለዱ ይታወቃል ።

ወገኖቻችን ! የሥጋና የነፍስ ነፃነት ወደምናገኝ በት ፣ የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስን ተከት ለን የማይጠፋ ሕይወት ወራሾች ወደምንሆንበት ወደ ሐዲስ ኪዳን ወደ ወንጌል ተጠርተናል ። ከአሮጌው ሥራችንና ከጨለማው ጉዞአችን እንመ ለስ ፣ ለእሪትና ለኃጢአት ከሚያስገዛ ክፉ ሥራችን ተለይተን በወንጌል እንኑር ። የሰላም ወንጌልን እንማር ፣ በሥጋዊ ፈቃድ ተስበን የነፍስ ነፃነት ለምናገኝባት ለወንጌል ምክንያት አንሻላት ። በፍ ጹም ፍቅር ሆነን በተፈጥሮ ከሚመስሉን ወንድሞ ቻችን ጋር ሁሉ በሰላም እንኑር ። «ወንድምህን እን ደራስህ አድርገህ ውደድ» የሚለው አንዱ ሕግ ሕግ ጋቱን ሁሉ ይፈጽማልና ። በነፍሳችን ፈቃድ ለመ ኖር እንትጋ ፣ ለሥጋችን ፈቃድ አንቸነፍ ፣ የፈቃዳ ችን ገዥዎች እንጂ ተገዥዎች አንሁን ። ነፍስ ልት ሠራ የማትወደውን ሥጋ ሊሠራ ይወዳል ። ነፍስም ሥጋ ሊሠራው የማይወደውን ልትሠራ ትሻለች ፤ እነዚህ የነፍስና የሥጋ ፈቃዳት እየተሳሳቡ በሰው ሕይወት ውስጥ ትልቅ ችግር ይፈጥራሉ ።

ስለዚህም የምንወደውን ትተን የማንወደውን እን ድንሠራ ያስገድዱናል ። በጎ መሥራት ፣ እውነት መፍረድ ፣ ሰላምን የመሻትና ፍቅርን የመከተል ዕውቀትና ፍላጎት በልቡናችን መኖሩ እየታወቀን የምንወደውን ትተን የማንወደውን ወደ መሥራት እናዘነብላለን ።

እውነተኛ የክርስቶስ ተከታይ ክርስቲያን ለመሆን በሚወደድ መልካም ሥራ ሰውንና እግዚአብሔርን ማገልገል ያስፈልጋል ። የነፍስ ፈቃድ ደስታ ፤ ልጅ ነት ፣ አንድነት ፣ ትዕግሥት ፣ በጎነት ፣ መረዳዳት ፣ ሃይማኖት ፣ ትንንት ፣ ንጽሕና ነው ። ከእግዚአብሔር መወለድ የልጅነትን ክብር ማግኘት የሚቻለው በነዚህ መሥመሮች ላይ በመጓዝ ብቻ ነው ። ከዚህ የሚበልጥ በጎ ሕግ የለም ። በመንፈስ ከእግዚአብ ሔር ለመወለድ ሰውነትን ለጽድቅና ለሰላም ከማይ ስማማ የኃጢአት ሥራ ማራቅ ያስፈልጋል ።

ሕጉን በማፍረስና ትእዛዙን ባለመፈጸም ለበ ደል ነው ለኛ ለሰው ልጆች ራሱን ካሳ አድርጎ ለመስጠት በሥጋ መገለጡን በምናስብበት ጊዜ የክርስቶስ ልደት ውስጣችንን የምንመረምርበትና በደላችንን የምንመለከትበት የጽድቅ መስተዋት መሆኑን እንገነዘባለን ። በዓለማችን ሲወዱት የመ ውደድ ብድር የሚመልስ እንጂ ሲጠሉት የሚወድ የለም ። በክርስቶስ የተሰጠው ትምህርትና መመ ሪያ ግን የሚወዱንን ብቻ ሳይሆን የሚጠሉንንም በመውደድ ወደፍቅር እንድንመለስ ነው ። በሌላው ያለውን ጉድፍ እጥርተን ማየትና መፍረድ የምን ችለው በክርስቶስ የጽድቅ መስተዋት አስቀድመን ራሳችንን ማየትና መመልከት ስንበቃ ነው ። በሌ ላው ዘንድ ሰላም እንዳለና እንደሌለ መናገርም ማስተማርም የሚቻለው በውስጣችን ሰላም መኖ ሩን መርምረን ስናረጋግጥ ብቻ ነው ። የእግዚአብ ሔር ሕጉ ትእዛዙ ፣ ምክሩ ጥበቡ ፣ ቅዱስ ፈቃዱና ትምህርቱ ሁሉ ለፍጥረት ሰላምና ደኅንነት ነው ። በልደቱ የመሠረተውም ሰላምን ነው ።

በጌታ ልደት በቤተ ልሔም አካባቢ የነበሩ እረ ኞች ከሰማያውያን መላእክት ጋር ሲዘምሩ ያደሩት በሰውና በእግዚአብሔር ፣ በምድራውያንና ሰማያ ውያን ፣ በሥጋውያንና መንፈሳውያን መካከል ስለ ተገኘው እርቅና ሰላም ፣ በዙሪያቸው ሲያበራ ስለ ታየው የእግዚአብሔር ክብር ነው ።

ስለሆነም በክርስቶስ ልደት የተመሠረተውን እር ቅና ሰላም በተግባር የምንገልጽበት በክርስቶስ የተ ገኘውን ሰላም ለሁሉ የምንሰብክበት ጊዜው አሁን ነው ።

በዐሉን የሰላምና የደስታ በዐል ያድርግልን ።



# "ሰላም በምድር"

"ክብር ለእግዚአብሔር በሰማያት ይሁን በም ድርም ሰላም ለሰው ልጆችም በጎ ፈቃድ"

ይህ የሰላም ዐዋጅ መድኅኔ ዓለም ክርስቶስ በተ ወለደበት ዕለት የተነገረ ነው ። በሰዎች አንደበት ሳይሆን በሰማይ የመላእክት ሠራዊት የተነገረ የሰ ላም ዐዋጅ ነው ። ከሰዎች መካከል ሰላም አልነ በረምና ስለ ሰላም ሊናገር የሚችል ማንም ሰው አልተገኘም ።



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ልሔም እንደተወለደ

በዚህም የተነሳ የሰላሙን ዐዋጅ ለሰው ልጆች ይና ገሩ ዘንድ መላእክትከሰማይ ወደ ምድር ተላኩ ፤

አምላክ በምድር ላይ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሲወለድ መላእክት በምድር ላይ "ክብር ለእግዚአብ ሔር በሰማያት ይሁን " እያሉ ሲዘምሩና ሰላምን ለ ሰው ልጆች ሲያበሥሩ ምድር ሰማይ ሆነች ። ክብርና ሰላም በሰማይ እንደሆኑ በምድር ሆኑ ፤ የእግዚአ ብሔር በጎ ፈቃድ በሰማይ እንደሆነ እንዲሁም በም ድር ሆነ ።

በእግዚአብሔርና በሰዎች ፣ በመላእክትና በሰዎች እንደዚሁም በሰዎች መካከል ሰላም በመጥፋቱ ሰዎች ከእግዚአብሔር ተለይተው ነበር ። እግዚአ ብሔርም ከሰዎች በረድኤት ርቆ ነበር። መላእክትም ሰዎችን ለማገልገል አልቻሉም ነበር ።

ነገር ግን የሰላም አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በተወለደ ጊዜ እግዚአብሔር ሰዎችን ታረቀ የሰው ልጆችም ከእግዚአብሔር ይቅርታን አገኙ ፣ መላእክትና ሰዎች በአንድነት እግዚአብሔርን አመ ሰገኑ ።

በኃጢአት ጨለማ ውስጥ ይኖር ለነበረው ሕዝብ እውነተኛው የዓለም ብርሃን ሲገለጥ ሁከትና ሽብር፣ ድንጋጤና ፍርሃት በሰፈነበት ፤ የሰይጣን አገዛዝ ቀንበር ከብዶ በነበረበት ዘመን እውነተኛው የነፃ ነት ጌታ የሰላም ንጉሥ ክርስቶስ ሲወለድ ሰላም በም ድር ተብሎ ታወጀ ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት ዕለት ከላይ ከአርያም የታወጀውም ሰላም ለዚች ለም ንኖርባት ምድር ማስፈለጉ ታወቀ ። እግዚአብሔር ምድርን ሲፈጥራት ወተትና ማር እንድታፈስ ነበር። የሰው ልጆችም የተፈጠሩ የዚሁ በረከት ተጠቃሚዎ ች እንዲሆኑነበር ነገር ግን ሰዎች የሰላምን ጠቃሚታ በውል ባለመገንዘባቸው ዓለም የጦርነትና የእምባ ጎሮ መድረክ ለመሆን የተቃረበች ትመስላለች ።

የሰማይ መላእክት ሰላምን የተመኙላት ይህች ዓለም ከሽብር ከፍርሃትና ከድንጋጤ ነፃ እንድትሆን ከደም እንድትጠራ ሰዎች ሁሉ እንደ መላእክት ከመላእክት ጋር "ሰላም በምድር" ሰላም በዓለም በማለት ድምፃቸውን ማሰማት ስለ ሰላም እጆቻ ቸውን ወደ እግዚአብሔር ለጸሎት ማንሳት ይኖር ባቸዋል ።

የዓለማችንን ማኅበራዊ ሕይወት ከሚያደፈርሱት ምክንያቶችአንዱ የሰላም መታጣት መሆኑ ግልጽነው ሰላም ያላቸው ሕዝቦች የተረጋጋ ሕይወትና ብልጽ ግና የተመቻቸ ዕድል ይኖራቸዋል ሰላም የዕድገትና የብልጽግና ለሰው ልጆችም የኑሮ መሻሻል መሠ ረት ነውና ።

ሰላም ሲባል የጦር መሣሪያ መቀነስና የጦርነቶች መቆም ብቻ አይደለም ። ጦርነትን የሚጋብዘው ጥላቻ ከሰዎች መካከል መወገድ አለበት ። ፍቅር አንድነትም እንዲኖር ያስፈልጋል ። ሰላም የሚያስ ገኛቸው መልካም ነገሮችን ሁሉ ሰዎች ሲያገኙ ሰላም በሰዎች መካከል ሊኖር ይችላል ።

እውነተኛና ትክክለኛ እኩልነት ሲኖር የሰው ልጆ ችም መብት ሲጠበቅ ሚዛናዊ ፍትሕ ሲሰጥ በሰው ልጆች መካከል ሰላም ይመሠረታል ።

ሆኖም ሰላም ሊገኝ የሚችለው ከእግዚአብሔር ነው ። እግዚአብሔር የሰላም አምላክ ነውና ። በመ ሆኑም ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት ሲኖ ራቸው ሰላምን ያገኛሉ ። ከእግዚአብሔር ጋር ሲታ ረቁ እርስ በርሳቸው ይታረቃሉ ።

ክርስቶስ በተወለደበት ዕለት በመላእክት የታወ ጀው ሰላም ሊገኝ የሚችለው ሰው ሆኖ በተወለደው በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው ።

"ወደ ወገኖቹ መጣ ወገኖቹም አልተቀበሉትም ለተቀበሉት ግን የእግዚአብሔር ልጆች እንዲባሉ ሥልጣን ሰጣቸው " እንደተባለ ክርስቶስን የሚ ቀበሉ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው ። የእግ ዚአብሔር ልጆች የሰላም ልጆች ናቸው «ሰላምን የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና" ።

መጋቢ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ



www.ethiopianorthodox.org

# እንደገና መወለድ

«ዳግመኛ ያልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግሥት አያያትም (መንግሥተ ሰማይን አይወርስም») ዮሐ ፣ ፫ ፣ ፫)

ይህ ቃል የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ነው ።

እንደገና ወይም ዳግመኛ መወለድ የሚለው ቃል ለኒቆ ዲሞስ የ ገለጸው የሥጋ ልደትን ሳይሆን ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ ከማሕጸነ ዮርዳኖስ መወለድን ነው ።

ጌታችን በዚህ ለኒቆዲሞስ በአስተማረው ትምህርቱ ከመንፈስ ቅዱስ መወለድ የሚቻለው በማየ ገቦ ኢየሱስ በመጠመቅ እንደሆነና ከእግዚአብሔር በጥምቀት ያልተወለደም የእግዚአብሔርን መንግሥት እንኳን መውረስ ማየት እንዳማይቻለው ገልጦልናል ። በሌላም ቦታ «ያመነ የተጠመቀ ይድናል ያላመነ ያልተጠመቀ ግን ይፈረድበታል» ብሏል (ማር ፲፮፣፲፮) ።

ዳግመኛ ያልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም የ ሚለውም ከዚህ ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው ። ምክንያቱም ዳግመኛ መወለድ መጠመቅና ከእግዚአብሔር መወለድ እንደመሆኑ ያላመነ ያልተጠመቀ ከእግዚአብሔር ያልተወለደ ነውና እንደማይድንና ከአልዳነም መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ እንደማይችል ስለተነገረ ነው ።

ይህ ከእግዚአብሔር የመወለድ ዕድል የተገኘውም በሃይማኖት ነው ። ክርስቶስን አምላክ ወልደ አምላክ ነው ብሎ በሃይማኖት ያልተቀበለ ከእግዚአብሔር መወለድ አይችልም ። ይህ ጸጋ የተሰጠ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክ ወልደ አምላክ ብሎ ለአመነና በሃይማኖት ለተቀበለ ነው ። ስለዚህ ነው ወንጌላዊው ዮሐንስ « ሰውን በአርአያችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር ብሎ ወደ ፈጠራቸው ወገኖቹ ወደ አዳም ልጆች ፤ የበኵር ልጆቼ ናችሁ ወደ አላቸው ወደ እሥራኤል መጣ ። እነሱ ግን አልተቀበሉትም ማለት አላመኑበትም ላመኑበት ግን በስሙ ያመኑ የእግዚአብሔር ልጆች ይባሉ ዘንድ ልጅነትን ሰጣቸው በዚህ መንፈሳዊ ልደታቸው ከሥጋዊ ከደማዊ ግብር ወንድና ሴት ተዋደው ከሚሠሩት ሥራም ያልተገኙ ናቸው በመንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ተወልደዋል እንጅ» ብሎ የጻፈው (ዮሐ ፩፣ ፲፩—፲፫ )

በጌታችን በመድኃኒታችን ትምህርት መሠረት ሁለተኛ መወለድ ማለት እንደገና ወደ እናት ማኅጸን ተመልሶ በሥጋዊና በደማዊ ፈቃድ መወለድ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ረቂቅ ልደት የነፍስ ልደት መወለድ መሆኑ ታውቋል ።

ከእግዚአብሔር የመወለድም ጸጋ የሚገኘው በጥምቀት መሆኑ ተረጋግጦአል ። ይህ ከሆነ ጥምቀት ምንድነው ? እንዴት ተመሠረተ ? ጥምቀት እንዴት ተያይዞ መጣ ? የጥምቀት ዓይነቱ ስንት ነው ? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ወደ መሠረቱ ተመልሰን እንመልከት ።

ጥምቀት ሌሎቹን ምሥጢራት ለመሳተፍ የቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን የመጀመሪያው መግቢያ በር ነው ።



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእደ ዮሐንስ ሲጠመቅ

በጥምቀተ ክርስትና የምንጠመቀው ጥምቀት የተመሠረተው በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነው ።

ክርስቶስ ጥምቀተ ክርስትናን ከመመሥረቱ በፊት በብሉይ ኪዳን የአይሁድ ጥምቀት ፤ የዮሐንስ ጥምቀት በመባል የሚታወቁ ሁለት ዓይነት ጥምቀቶች ነበሩ የአይሁድ ጥምቀት የማንጻት ጥምቀት ሲባል የዮሐንስ ጥምቀት ግን የንሥሐ ጥምቀት ተብሎ ይጠራል ።

የአይሁድ ጥምቀት ዓላማ ጣኦት አምላኪ የሆነውን የአሕዛብ ወገን አስተምረውና አሳምነው ወደ ኦሪት ሃይማኖት ሲመለሱ ከርኵሰት ከጣኦት ለማንጻት ከግዝረት ጋር ያደርጉት የነበረ ጥምቀት ነው ። (ማቴ ፳፫ - ፲፭)

ለምሳሌ በቃና ዘገሊላ ሠርግ ውሀ የተሞላባቸው ስድስት ጋኖች አይሁድ ያጠምቁባቸው የነበሩ ጋኖች እንደሆኑ ተጽፎዋል (ዮሐ ፪-፮) የዮሐንስ ጥምቀት ዓላማ ደግሞ በትዕቢት በክህደት በአምልኮተ ጣኦት የጨለመው የሰው ልጅ ልቡና በአምልኮተ እግዚአብሔር በሃይማኖት በቅን ልቡና በትሑት ሰብእና ተመልሶ ክርስቶስን ለመቀበል እንዲችል ለንስሐ የሚያዘጋጅ ነበር ። (ማቴ ፫ ፣ ፩—፲፪ ።

የጌታችን የመድኃኒታችን ጥምቀት ግን ከሁለቱም የተለየ ኃጢአትን የሚያስተሠርይ ከእግዚአብሔር ፣ የመወለድን ጸጋ የሚያስገኝ የልጅ ነት ጥምቀት ነው ።

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ በ፴ ዓመቱ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ ጥምቀትን መሠረተ ።



ዘንድ ሜዳ የጥምቀት በዓል አከባበር የካህናቱ ዝማሬ

ስለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት ቀደም ብሎ በምሳሌና በትንቢት በብሉይ ኪዳን ተነግሮዋል ።

ለምሳሌ በዮርዳኖስ ስለመጠመቁ የተነገረውን ትንቢት ቀጥሎ እንመልከት ፤

፩ኛ/ «ባሕር አየች ሸሸችም ዮርዳኖስም ወደ ኋላው ተመለሰ ተራሮች እንደ ኮርማዎች ኮረብቶችም እንደ ጠቦቶች ዘለሉ ። አንቺ ባሕር የሸሸሽ አንተስ ዮርዳኖስ ወደኋላህ የትመለስህ ምን ሆናችኋል ? እናንተስ ተራሮች እንደ ኮርማዎች ኮረብቶችስ እንደ ጠቦቶች ለምን ዘለላችሁ ? ከያዕቆብ አምላክ ፊት መዝ (፩፻፲፫ ፣ ፫—፯)

፪ኛ/ «አቤቱ ውሃች አዩህ ውሆችም አይተውህ ፈሩ ጥልቆች ተነዋወጡ ። ውሆችም ጮሁ» መዝ ፸፮ ፡ ፲፮ )

፫ኛ/ «የእግዚአብሔር ቃል በውሆች ላይ ነው የክብር አምላክ አንጐድጐደ እግዚአብሔር በብዙ ውሆች ላይ ነው» (መዝ ፳፰፣ ፫)

በዚህ የትንቢት ቃል መሠረት «ባሕር አየች ሸሸችም «ውሀዎች አይተውህ ፈሩ » እንደ ተባለው የያዕቆብ አምላክ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመጠመቅ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሲገባ ከታች ያለው ባሕር ሸሽቶ ወደፊቱ ሲሮጥ ከላይ ያለው ፈሳሽ ወደኋላው ተመልሷል ። ይህንንም አርከ ድንግል የተባለው የሀገራችን ሊቅና ደራሲ አርኬ በተባለው ድርሰቱ «ሰላም ለማየ ዮርዳኖስ ዮሐንስዘአተቦ ፤ መንፈስ ቅዱስ ከመ አጥበቦ ፣ ሶበ መጽአ ቃል እምሰማይ ለተናብቦ ። ነድ ለማየ ባሕር ከበቦ ። ማይ ኅበ የሐውር ጸበቦ» ብሎ ገልጦታል የዚህም ዐርኬ ትርጉም «መንፈስ ቅዱስ እንደ አመለከተው ዮሐንስ ለዓረከው ለዮርዳኖስ ውሀ ሰላምታ ይገባዋል ። ቃል (ወልድ) ለመነጋገር ከሰማይ በመጣ ጊዜ ነድ (እሳተ መለኮት) የባሕሩን ውሀ ከበበው ውሃም የሚሔድበት አጣ ጨነቀው» ማለት ነው ።

«የእግዚአብሔር ቃል በውሆች ላይ ነው» የሚለውም የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው የሆነው ወልድ በዮርዳኖስ ወንዝ መጠመቁን ያሳያል ። ነቢዩ በትንቢታዊ ቃሉ «የእግዚአብሔር ቃል ያለውን በተከታዩ መስመር» እግዚአብሔር በብዙ ውሀዎች ላይ ነው በማለት እግዚአብሔር ብሎ ጠርቶታል በዚህም አነጋገር የተጠመቀው ወልድ እግዚአብሔር መሆኑን አስተምሮዋል ። (ዮሐ ፩ ፡ ፩-፪፣፲፬ ። መዝ ፡ ፹፪ ፡ ፮ ።

ከዚህም በላይ የተገለጠው ስለጌታ ጥምቀት በትንቢት ከተነገረው ጥቂቱ ሲሆን ምሳሌው ደግሞ እንደ ሚከተለው ነው ።

፩ኛ/ ዮርዳኖስ ከላይ ምንጩ አንድ ነው ዝቅ ብሎ በደሴት ይከፈላል ከታች ወርዶ እንደገና ይገናኛል ። ዮርዳኖስ ከላይ ምንጩ አንድ መሆኑ የሰው ሁሉ ምንጭ አንድ አዳም መሆኑን ያሳያል (ዘፍ ፪ ፡ ፳፩-፳፫ ዝቅ ብሎ በደሴት መከፈሉ እሥራኤል በግዝረት አሕዛብ በቁልፈት እንዲሁም እሥራኤል በአምልኮተ እግዚአብሔር አሕዛብ በአምልኮተ ጣኦት መለያየታቸውን ያመለክታል (ዮሐ ፬ ፡፱ ዘዳ ፳፫ - ፲፩ ። ዘፍ ፲፯ ፳፫-፳፯ ። ዘዳ ፯ - ፩-፭ ። ከታች ወርዶ መገናኘቱ ሕዝብና አሕዛብ በክርስቶስ በጥምቀት አንድ መሆናቸውን ይተረጉማል (የሐ . ሥ ፬ ፡ ፴፪ ። ኤፌ ፬ ፡ ፬-፯ ።

አብርሃም አራቱን ነገሥተ ኮሎዶጐመርን ድል ነሥቶ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ሲሔድ መልከ ጸዴቅ ኅብስተ አኰቴት ጽዋዐ በረከት ይዞ ተቀብሎታል ። አብርሃም የምእመናን ፤ ዮርዳኖስ የጥምቀት ፤ መልከ ጼዴቅ የቀሳውስት ፤ ኅብስተ አኰቴት ጽዋዐ በረከት የሥጋው የደሙ ምሳሌ ነው ። (ዘፍ ፲፬ ፣ ፲፬-፳ ። መዝ ፻፱ ፣ ፬ ። ዕብ ፣ ፯ ፣ ፩-፲ ።

፫ኛ/ ንዕማን ኢዮብ በዮርዳኖስ ተጠምቀው ከደዌያቸው ድነዋል ። ፪ ፣ ነገ ፭-፩—፲፱ ። ሉቃ ፬-፳፯ ። ኢዮ ፣ ፵ ፣ ፳፫-፴፪ ። ፵፪ ፣ ፲ ። ኢዮብ ፣ ንዕማን የአዳምና የልጆቹ ፤ ደዌ የመርገመ ሥጋ የመርገመ ነፍስ ዮርዳኖስ የጥምቀት ምሳሌ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

፬ኛ/ እሥራኤል ዮርዳኖስን ተሻግረው ምድረ ርስት ገብተዋል ። እሥራኤል ዘሥጋ የእሥራኤል ዘነፍስ የምእመናን ፤ ዮርዳኖስ የጥምቀት ፤ ምድረ ርስት የገነት የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌዎች ናቸው (ኢያ ም ፤ ፫ -ቍ ፬ ።

፭ኛ/ ኤልያስ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ወደ ገነት አር ጓል (፪-ነገ ። ፩፡፯-፲፩ ። ኤልያስ የምእመናን ፤ ዮርዳኖስ የጥምቀት ፤ ገነት በቂሙ ምሳሌዎች ናቸው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮር

ጠመቁ ምሳሌ ለመሆን ነው ። «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ዮሐንስን» ውሀው እንዲባረክና ለሰው ልጆች መድኃኒት እንዲሆን በውሀ አጥምቀኝ ሲለው ዮሐንስ እኔ ከአንተ ልጠመቅ ይገባኛል እንጂ እን ዴት አንተ ወደእኔ ትመጣለህ ? አይሆንም ብሎ ከለ ከለው ጌታም «ይህ ለእኛ ተድላ ደስታችን ነው ጽድ ቅን ሁሉ ልንፈጽም ይገባናልና አጥምቀኝ» አለው ።

ይህ ለእኛ ተድላ ነው ማለት ትርጉሙ ፩ኛ / ጌታ ንና ዮሐንስን በ ሚመለከት አንተ መጥምቀ መለ



በጃንሜዳ በዐለ ጥምቀት የሰንበት ት/ቤቶች ተማሪዎች

ዳኖስ በመጠመቁም የአዳምና የሔዋን ስመ ግብር ናት (የባርነት ስም) የተጻፈበት ዕብነ በረድ ሁለት ሲሆን አንዱ የተቀመጠው በዮርዳኖስ ስለነበር ይህን የዕዳ ደብዳቤ እንደ ሰውነቱ ረግጦ እንደ አምላክነቱ አቅልጦ አጥፍቶታል ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትንቢትና በምሳሌ ስለጥምቀቱ የተነገረውን ለመፈጸም ዮሐንስ ፴ ዓመት ከመንፈቅ ሲሆነው እርሱ ጌታ ፴ ዓመት ሲሞ ላው መጥምቁ ዮሐንስ ሰዎችን ሰብስቦ በዮርዳኖስ የንሥሐ ጥምቀት በማጥመቅ ላይ በነበረበት ወቅት ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ወደ ዮሐንስ መጣ ። የጌታም ወደ ዮሐንስ መሔድ ለትሕትና ለአርአያነት ነው ጌቶች መጥታችሁ አጥምቁን እያሉ ቀሳውስትን ወደ ቤታቸው እንዳይጠሩ ራሳቸው ሒደው እንዲ

ኮት ተብለህ ክብርህ ይነገራል እኔም በአገልጋዩ እጅ ተጠመቀ ተብሎ ትሕትናዩ ይነገራል ለማለት ነው ።

፪ኛ/ አብ መንፈስ ቅዱስን በሚመለከት አብ «ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ይህ ነው ልጄ ብሎ ሲመ ስከር ፤ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥ አንድነት ሦስት ታውቋል ።

«ጽድቅን ሁሉ ልንፈጽም ይገባናል ማለትም ፩ኛ/ ትንቢተ ነቢያትን ልንፈጽም ይገባናል ማለት ነው ይኸውም ዮሐንስ እንዲያጠምቅ ክርስቶስ እን ዲጠመቅ ትንቢት መነገሩን ያሳያል ሚልክ ፫፣ ፩፣ ፭፣፯ ። ሉቃ ፩፣፲፮፣፲፯ ። ማቴ ፲፩-፲ - ፲፬ ። ዮሐ ፩- ፲፭-፴፬ ሉቃ ፫፣፩—፲፯ ። ማር ፩፣፩-፲፩ ። ፪ኛ በማኅ ጸን የጀመርነውን ቸርነት ልንፈጽም ይገባናል ማለት

ነው መርገመ ሥጋ መርገመነፍስ የጠፋ በማኅጸን ነውና ይኸውም በዘር የ ሚተላለፍ ኃጢአት ነው ። (ማቴ ፩፣፳፩ ።

ከዚህም በኋላ መጥምቁ ዮሐንስ «ሌሎችን ሳጠ ምቅ በአንተ ስም አጠምቃለሁ አንተን ሳጠምቅ ምን ልበል ብሎ ጌታን ጠየቀው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «ወልዱ ለቡሩክ ክግቱ ብርሃን ተሠሀለኒ በል» ብርሃንን የምትገልጥ የቡሩክ አብ የባሕርይ ልጁ ይቅር በለኝ እያልክ አጥ ምቀኝ ስለአለው ዮሐንስ ክርክሩን አቆመና አጠመ ቀው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውሀው ወጣ።ሰማያትም ተከፈቱና የእግዚ አብሔር መንፈስ እንደርግብ ወርዶ በርሱ ላይ ሲቀ መጥ አየ እነሆም ድምጽ ከሰማይ መጥቶ «በርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» አለ ብሎ ወንጌ ላዊ ይተርካል (የማቴ/ ም/፫- ቍ/ ፲፫-፲፯ ሰማያት ተከፈቱ ሲባል በሰማይ መከፈት መዘጋት ኑሮ ሳይ ሆን ምሥጢረ እግዚአብሔር ተገለጠ ማለት ነው ። ምሥጢረ እግዚአብሔር የተባለውም ምሥጢረ ሥላሴ ነው አካላቸው በብሉይ ኪዳን ቢገለጽም ስማ ቸውና ግብራቸው ግልጽ የሆነ በዮርዳኖስ ነውና ።

ጌታ ጥምቀትን ራሱ ከፈጸመ በኋላ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ በማለት ጥምቀተ ክርስትና ተመሥረተ (ማቴ - ፳፰/፲፱ የጌታን ጥም ቀት በየዓመቱ የምናከብረው ለመታሰቢያ ነው ። ጌታ በየዓመቱ የሚጠመቅ ሆኖ አይደለም ።

በመንፈስ ቅዱስ የ ሚያጠምቀው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጥምቀት ወደ ሥራው ሲገባ የክርስቲያን

ጥምቀት በመንፈስ በደም በውሀ ሆነ (፩-ዮሐ ፤ ፭ ፤ ፮-፰)

የደም ጥምቀት የ ሚባለው ፩ኛው ሥጋውን ደሙን የ ሚመለከት ሲሆን ሁለተኛው ደመ ሰማዕታት ነው ።

የውሀ ጥምቀት የሚባለውም ፩ኛው ማየ ገቦን የሚመለከት ሲሆን ሁለተኛው፤ እንብዐ ንሥሐ ነው።

በጥምቀት የ ሚገኘው ጸጋና ክብር ፩ኛ/ ከእግዚ አብሔር መወለድ ፪ኛ ከኃጢአት መንጻት ነው ። ሰው በጥምቀት ከኃጢአት በመለየቱ ከእግዚአብ ሔር በጸጋ በመወለዱ መንግሥተ ሰማይን ለመ ውረስ ይበቃል (ሕዝ ፤ ፴፮ ፤ ፳፭ ። የሐ ፤ ሥ ፤ ፪ ፤ ፴፰ ። ፩ ቆር ፮ ፤ ፲፩) «ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት (ጸሎተ ሃይማኖት) ። የእግዚአ ብሔር ጸጋ ለሰው ልጅ የ ሚሰጠው በጥምቀት በሥ ላሴ ሲወለድ መሆኑ በቅዱሳት መጻሕፍት በሰፊው ተጽፎዋል (ዮሐ ፫ ፤ ፭ ኤፌ ፭ ፤ ፳፮ ። የሐ ፤ ሥ ፲፱ ፫ — ፯ ። ቲቶ ፫ ፤ ፭ ። ፩ ፤ ቆር ፩ ፤ ፲፬-፲፫ ። ፩ ፤ ጴጥ ፩ ፤ ፫—፯ ። ገላ ፬ ፤ ፭-፯ ።

የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር የመወለድ ጸጋ የሚ ያገኝበት ከእግዚአብሔር በመወለዱም መንግሥተ ሰማይን የ ሚወርስበት ታላቁ የድኅነት በር ጥምቀት መሆኑን ሁላችን ከአወቅን ወገኖቻችንን ለማጻንና ለርስተ መንግሥተ ሰማያት እንዲበቁ ለማድረግ ያላ መኑትና ያልተጠመቁት በተዋሕዶ ሃይማኖት ክርስ ቶስን አምነው እንዲጠመቁ እናድርግ እንዚህን ከክርስትና ሃይማኖት ውጭ ሆነው የሚገኙ ወን ድሞቻችንና እኅቶቻችን ለማጥመቅም በቂ ሐዋር ያትን እናዘጋጅ ።

ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ
የትምህርትና ማሠልጠኛ መምሪያ ኃላፊ

www.ethiopianorthodox.org

# የመጀመሪያው ተአምር

**ዮሐንስ ወንጌል** ሁለተኛ ምዕራፍ የምንመለከተው በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመውን የመጀመሪያ ተአምር ነው ።

**ቅድመ ልደተ** ክርስቶስ በነበሩ ነቢያት ብዙ አስደናቂ ተአምራት ተደርገዋል ። በሙሴ ጊዜ በፈርኦን የጭካኔ እገዛዝ ሲማቅቅ ፤ በዋይታና በዕንባ ወደፈጣሪው ሲያመለክት የነበረውን ሕዝብ ከባርነት ቀንበር ለማላቀቅ በምድረ ግብጽ ከተፈጸመው የቅጣትና የምሕረት የኃይል ተአምራት ሌላ ታላቁ ቀይ ባሕር ከሁለት ተከፍሎ ሕዝበ እግዚአብሔር በደረቅ ምድር ተሻግሯል ። ፈጣሪው የ ሚመራውን ሕዝብ በጉዞው ለመበቀል በክንዱ ተማምኖ የተከታተለው ፈርኦን ግን ከነሠራዊቱ ሰጥሞበታል ። በምድረ በዳው ጉዞ የመንገደኛውን ሕዝብ ችግር የሚያስወግዱና ክፋሳንት ጋር የተያያዙ ተአምራት ተደርገዋል ፤ መና ከደመና ወርዶአል ፤ ውሀ ከምንጭ ፈልቋል ፤ መራራ የነበሩ የወንዝ ፈሳሾችም እየጣፈጡ ለመጠጥ አገልግሎት ውለዋል ።

የቃና ዘገሊላው የኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያ ተአምርም የሰዎችን ችግር ሐፍረትና ጭንቀት ከማቃለል ጋር የተያያዘ ታሪክ አለው ። መድኅን ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በኅብረተሰብ ማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ በመገኘት ውሀውን ወደወይን ለውጦ በሠርጉ ቤት ደርሶ የነበረውን ሐፍረትና ጭንቀት አስወግዶአል ።

ጊዜው ከዮርዳኖስ ጥምቀትና የዓርባ ቀን የጾም ተጋድሎ በኋላ ጌታ ወደሕዝብ መውጣት ጀምሮ በናዝሬት ገሊላ በገባበት ሦስተኛ ቀን ፤ ቦታው የገሊላ ክፍል በምትሆን በቃና መንደር ነው ።የሰውን ልጆች ጭንቀትና ኀዘን ወደ ደስታ ለመለወጥ ከጨለማ ወደ ብርሃን ፤ ከሞት ወደ ሕይወት ለማሸጋገር በዓለም ላይ የተገለጠው ጌታችን መድኅኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሕዝብ መገለጥ በጀመረበት ጊዜ የተገኘውና የመጀመሪያውን ተአምር ያደረገው በሠርግቤት ነው ።

የጌታ መምጣት ከዮሐንስ መጥምቅ የተለየ ነው ዮሐንስ የጌታን መንገድ ለመጥረግና ለማስተካከል ከበረሃ ወደ ሕዝብ በተገለጠ ጊዜ ሲበላና ሲጠጣ አልታየም ። በዚህም የማያስበላ የማያስጠጣ ችግር አለበት ተብሎ ታምቶአል ። በኅብረተሰቡ ውስጥ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ከሚታዩትና የተዋረደ ግምት ከሚሰጣቸው ወገኖች ጋር በላ ጠጣ የሚለው ሐሜት ባይቀርለትም ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሊፈልገውና ሊያድነው ከመጣለት ሕዝብ ጋር እየበላ እየጠጣ ነው ሕይወትነቱን ያረጋገጠው። በዓለም ላይ የሰውን ባህርይ ከመሸከም የሚከብድ ነገር የለም ። ቢበሉ ቢጠጡ በደለኛ ቢጾሙ ቢጸልዩ ሕመምተኛ ሙሾ ቢያወርዱለት የማያለቅስ ፣ ቢያቀኑ ቅኑለት የማይዘፍን ! ሲረዱት ሊተረጉሙት የሚረቅ የሰው ባሕርይ ! ሁሉን መሸከም የሚችለው ጌታ ግን የኅብረተሰቡን ባህላዊና ማኅበራዊ ሕይወት በውስጡ በመገኘት ብቻ ሳይሆን ፤ በሂደቱ ያጋጠመውን ችግር በማቃለል ፤ ኀዘንን ወደ ደስታ በመለወጥ በገቢረ ተአምር ባርኮታል ። ክብርና ሞገስ አጎናጽፎታል ። ጭንቅና ችግር በደረሰበት ቦታ የእግዚአብሔር ታዳጊነትና ክብር እንደዚህ ፈጥኖ ሲገለጥ ምንኛ ደስ ይላል ! የቃናው ሠርግ ቤት ውሀ ወደወይን ተለውጦ አስደናቂ ተአምር የታየበት ብቻ ሳይሆን ፤ የኅብረተሰብ ምንጭ የሆነው የሕጋዊ ጋብቻ ክቡርነትም የተረጋገጠበት ነው ።

በሠርጉ የቅድስት ድንግል ማርያምና የሐዋርያት በክብር እንግድነት ታድሞ መገኘት ለጋብቻ ሞገስ የሚሰጥ ሌላው ዐቢይ መልእክት ያለበት ቁም ነገር ነው ።

ቤተ ክርስቲያን በተፈቀደው ሕግ የተከሊልን ጋብቻ በግልጽና በጉባኤ የምታስፈጽመው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገኝበት የጸሎት ሥነ ሥርዓት መሊያየት የማይኖርበትን ቃል ኪዳን በይፋ ለማጽናት ነው ። ከዚህ ታሪክ ሊማሩት የሚገባ ብዙ ምሥጢር አለ ። የቤተሰብና ኅብረተሰብ መገኛ የሆነው ጋብቻ በጌታ ቡራኬ መሠረቱ የጸና ቃል ኪዳኑ የጠበቀ መሆን ይኖርበታል ። የጋብቻው ጸሎት ሰማያዊውን የበረከት ጌታ ወደሠርጉና ወደ ሰው ልጆች ማኅበራዊ ሕይወት የሚጋብዝ መልእክተኛ ነው ።

እንደየቤቱና የኑሮ ደረጃው አቅም በፈቀደ መጠን ቤት ሙሉ መደገስ ፤ ወይንና ፍሪዳ አዘጋጅቶወዳጅ ዘመድን ማስተናገድ ፤ ለሙሽሮችና ሚዜዎች እስከ ሣምንት የሚበቃ ድግስ ማዘጋጀት በሀገራችንም እስከ ቅርብ ጊዜ የተለመደ ሆኖ ቆይቶአል ። ኮክቴልና ሪሴፕሽን ሳይመጡና ሳይለመዱ ፣ የቃናው ሠርግ ቤት ሙሉ የተደገሠበት ነበር ። ግን የታደመው እንግዳ ሳይሸኝ ወይኑ አለቀ ፤ ባለቤቱ ድንጋጤ ላይ ፤ ተጋባዡ ሐፍረት ላይ ወደቀ ። ጋንን በርሜልን በማጫለጥ ወይም በመሸታ ግዥ ለመሸፈን የሚግደረደሩበት አማራጭ አልነበረም ። ይህ ዓይነቱ ችግር በቂና የተሟላ ሕይወት (ኑሮ አለን) ብለው የችግር ወሬ ሊሰማባቸው በማይፈልጉ ወገኖች አካባቢዎችም እንደዚሁ ባልታሰበና ባልተጠረጠረ ጊዜ የሚደርስ መሆኑን ያስገነዝባል ። ሁሉ ስጦታ ያለው የአምላክ ርዳታ የሚፈለገው ያን ጊዜ መሆኑን ያሳያል ።



www.ethiopianorthodox.org

ርኅርኅርተ ኅሊና ድንግል ማርያም የማማለድ ሥራዋን የጀመረችው በዚያ የሐፍረት ደመና በዞረበት የሠርግ ዳስ (ድንኳን) ውስጥ ነበር ። «- - - ወይናቸው አልቆባቸዋል» የሚለውን አቤቱታ ለልጅዋ ኢየሱስ ክርስቶስ አቀረበች ፤ ፀሠርጉ ባለቤቶች ችግር ውስጥ የጌታ ረድኤት እንዲደርስ አሳሰበች ።

— የወዳጆቻችንና ወገኖቻችንን ችግር መካፈል ፤ በራሳችንም የሌላው የጭንቅ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር በጸሎት የመማጸንን ጥበብና ግዴታ ያስተምራል ።

ለድንግል እመቤት የተሰጠው ምላሽ ቀጥተኛ አልነበረም ። የቁጣ አነጋገር በሚመስል ቃል «አንቺ ሴት ካንቺ ጋር ምን አለኝ ! » የሚል ነው ።

፩— በፍጡር ኅሊና ከመታሰቡና ከመነገሩ አስቀድሞ ያለውን አሳብ የሚያውቅ ፤

፪— ሳይለምኑትና ሳይጠይቁት ፍጡር ሁሉ በተፈጥሮ የሚያሻውን አውቆ የሚሰጥ እንጂ ሌላ ኃይል አሳስቦ ሊያሰራው የማይችል በአምላክ ነቱ አገብሮ — ማስገደድ የሌለበት መሆኑን የሚያስተምር ነው ። ምን ጊዜም ቢሆን ወደፈጣሪ በምናቀርበው ጸሎትና ልመና የተፈጥሮ ደረጃችንና የ ፍጡር አቅማችንን በመረዳት «ወይኩን ፈቃድከ - ፈቃድህ ይሁን» ብለን የሱን ፈቃድ መጠየቅና መጠበቅ እንጂ የኛ ፈቃድ ይሁን ብለን ማስገደድ እንደማንችል ያስተምራል ።

ቀጥሎ የተሠነዘረው ኃይለ ቃል «ጊዜዬ ገና አልደረሰም» የሚል ነው ። ምንጊዜም እግዚአብሔር ሥራውን የሚሠራበት ጊዜ የተወሰነ ነው ። በሰዎች ኅሊና የሚመረመርና የሚታወቅ አይደለም ። ይህ አበባል ግን በአንድ ገጹ «ተአምራት የማደርግበት ገና ነው» ማለትን ሲያመለክት በሌላ በኩል በወቅቱ ስለሚፈጸመው ተአምራት የሚያጠራጥር ምክንያትና የሚጠራጠር (ሰው) እንዳይኖር የወይኑ ጭልጥ (ምጥጥ) ብሎ ማለቅ በሁሉም ዘንድ እስከ ሚረጋገጥ መሆኑን ያመለክታል ።

«አንቺ ሴት - - »የሚለውም አነጋገር «ውሀውን ጠጅ አድርግላቸው» ስትይኝ «አይሆንም» እልሽ ዘንድ ካንቺ ጋር ምን ፀብ አለኝ ? በሠርግ ቤት የተገኘ ሁትስ ይኸን የመሰለውን ተአምር ላላደርግ ነውን ? ተብሎ ይተረጐማል ።

«አንቺ ሴት» የሚለውም አነጋገር ብቻውን የቁጣና የማራቅ ወይም የተግሳጽና የማሳፈር እመልክከት ያለበት ሳይሆን ፤ በአይሁድ ኅብረተሰብ የተለመደ የአክብሮትና በኛም ሀገር እመየቴ ፤ እመቤት ሆይ ፤ በሚል የአክብሮት አጠራር እንደሚታወቀው ያለ ሆኖ ጌታችን የተጠቀመው የማኅበረሰቡን ባህላዊ አነጋገር ዘይቤ ነው ። ይህንንም በ/ማቴ ፲፭-፳፰ ፤ ዮሐ ፬-፳፩ ፤ ፲፱-፳፮ ፤ ፳ ፡ ፲፭/ ይመለከቷል

ቅድስት ልጅዋ ለልመናዋ ምላሽ እንደማይነፍጋት በማወቅ ፤ ተአምራቱን በማመን ያቀረበችው ጥያቄ ስለሆነ አያይዞ « የሚያዛችሁን ሁሉ አድርጉ» በማለት ለሠርጉ ባለቤትና አስተናባሪዎች ላስተላለፈችው መልእክት የተከተለው መልስ «ጋኖቹን እስከአፋቸው ድረስ ውሀ ምሉአቸው» የሚል ነበር ። ይህም ከእመቤታችን ለቀረበው ልመናና ምልጃ ምንም ማስተሐቀር ነቀፌታ ሳይኖር ተቀባይነት አግኝቶ መፈጸሙን ያመለክታል ። የጌታ ጸጋና ቃል ኪዳን ስንኳን በማሕጸኗ ለተሸከመችው ንጽሕት ቅድስት ድንግል እናቱ በተለያየ ተልእኮ ላገለገሉትና በውነት ለተከተሉት ሁሉ የተረፈ ነው ። ማቴ- ፲ ፡ ፵ — ፵፪

ስድስቱ የወይን ጋኖችም በጥንቃቄ ከተመሉና ከተሠፈሩ በኋላ ውሀው በተአምር ተለውጦ ባለሠርጉ አዘጋጅቶት ከነበረው የበለጠ ጣዕምና ቃና ያለው ወይን ጠጅ ሆነ ። ባለቤቱ ፣ ቤተሰቡና ወዳጅ ዘመዱ ሁሉ ተደሰቱ። ተጋባዡም የወይኑ ጣዕምና ቃና መጣፈጥ መጀመሪያ ከነበረው የበለጠና የተወደደ በመሆኑ «ብዙ ሰው በድግሡ አስቀድሞ መልካሙን ያቀርባል ፤ ከጠገቡ በኋላ ግን ቢጠጡ ይጠጡት ባይጠጡት ይተውት ብሎ መናኛውን ያቀርባል አንተ ግን ቀለል ያለውን አስቀደምህ በመጨረሻም የተሻለውን አቀረብህ ፤ » በማለት እየቀመሱ በአድናቆትና ምሥጋና ገልጸውታል ።

ይህ የመጀመሪያ ተአምር በድግሡ የተካፈለውን ሁሉ ወደ እምነት የጠራ ይልቁንም በመንፈሳዊ ዕውቀት አእምሮአቸው ያልጎለመሰ ሐዋርያትን በእምነት እንዳጠናከረ ግልጽ ነው ። መድኅነ ዓለም ክርስቶስ ይህን አስደናቂ ተአምር ያደረገው ጊዜው ገና ሳለ የቅድስት እናቱን ልመና ለመፈጸም ሲል እንደሆነ ከቃሉ መረዳት ይቻላል ። ለቅዱሳን የተሰጠውን የማማለድ ክብር ፣ ጸጋና ቃል ኪዳን የሚለውጥ ሳይሆን ፣ በእናትና ልጅ መካከል ያለና የሚኖር የቤተሰብ ቋንቋ ነው ። «ቅድስት ድንግል ማርያም አታማልድም» ከሚለው ጥራዝ ነጠቅ ስብከት ጋር ዝምድና የለውም ።

ቀሲስ ዳኛቸው ካሣሁን

# ዝርወተ ዐጽሙ

የጌታችን ደቀ መዛሙርት ክርስትናን በዓለም ላይ በሚያስፋፉበት ጊዜ አረማውያን ልዩ ልዩ ፈተናና ጸዋትወ መከራ ፈጽመውባቸዋል ፤ የክርስቲያኖች ጠላት የነበሩት የሮም ነገሥታትም አሳዛኝና አሰቃቂ በደል አድርሰውባቸዋል ። ከአውሬዎች ጋር አታግለዋቸዋል የአውሬዎች ምግብ አድርገዋቸዋል ። በሠይፍ ስለት ቀልተዋቸዋል ። ለሰማይ አዕዋፍ ሲሳይ አውለዋቸዋል ። በምተር ቆራርጠው ፈጭተዋቸዋል ። በነፋስ ኃይል በትነዋቸዋል ቆዳ




ሊቀ ሰማዕታት ቅ/ ጊዮርጊስ

ቸውንም እንደ ሌጦ ገፈዋቸዋል ። በዚህም መልክ ሰማዕትነት የተቀበሉ ብዙዎች ናቸው ከነዚህም አንዱ ሊቀ ሰማዕታት ቅዱስ ጊዮርጊስ ነው ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ በፍልስጥኤም አውራጃ ተወለደ የቅዱስ ጊዮርጊስ አባት አንስጣስዮስ ፤ እናቱም ቴዎብስታ ይባላሉ ። የአባቱ አገር ቀጰዶቅያ ይባላል። የቅዱስ ጊዮርጊስ ወላጆች ደጋግ ክርስቲያኖች ፤እግዚአብሔርን የ ሚፈሩ ሰውንም የሚያከብሩ በተቀደሰ ትሩፋት ያስመሰከሩ እንደነበሩም የሰማዕቱ ገድል አረጋግጦላቸዋል ።

ለአንስጣስዮስ በዘመኑ የነበረው ንጉሥ ዱድያኖስ ከፍተኛ የሆነ ሹመት ሰጥቶት ነበር ። ነገር ግን ቅዱስ ጊዮርጊስ በተወለደ በሃያ ዓመቱ አባቱ አንስጣስዮስ ሞተ ። ቅዱስ ጊዮርጊስም ከኃዘኑ ከተጽናና በኋላ የአባቱን ሹመት ለመጠየቅ ወደ ዱድያኖስ ሄደ ። ከንጉሡ ድዱያኖስ አደባባይ እንደደረሰም ንጉሡ ከነ መኳንንቱ ከነመሣፍንቱና ከነሠራዊቱ ጣዖት አቁሞ ሲሰግድና ሲያሰግድ አገኘው ። ቅ/ ጊዮርጊስ ዱድያኖስ ይህንን አስነዋሪና አስቀያሚ ተግባር ሲፈጽም በማየቱ እጅግ ተበሳጨ በጣምም አዘነ ።

እግዚአብሔር አምላክም ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑሩህ በሰማይ ካለው ፤ በታችም በምድር ካለው ፤ ከምድርም በታች በውኃ ካለው የተቀረጸም ምስል ለአንተ አታድርግ ያለው ትእዛዝ በመፍረሱ ቅ/ጊዮርጊስን አሳዘነው (ዘጸአ ፳—፫-፬)

ከዚህም ጋር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ልትሆን ብትወድ ሂድና ያለህን ሻጠህ ለድሆች ስጥ ፤ መዝገብም በሰማይ ታገኛለህ ፤ መጥተህም ተከተለኝ፤ ብሎ የተናገረውን መስቀሉን ተሸክ ሞ ሊከተል ወሰነ ማቴ - ፲ ፣ ፴፱ ። ቅዱስ ጊዮርጊስ ይህ ዓለም ከንቱ ጠፊና ኃላፊ መሆኑን በጥልቀት መርምሮ ከተገነዘበ በኋላ ጣዕሙንና ፍቅሩን ንቆ የሥጋን ረብ ጠልቶ የመንፈስ ሠይፍ ታጥቆ ተነሣ ። (ኤፌ ፮— ፲፮-፲፯)

በዚህም መሠረት ቅዱስ ጊዮርጊስ ከአባቱ ከአንስጣስዮስ የወረሰውን ሀብት ሁሉ ለችግረኞች አከፋፍሎ ሰጠና እንደገና ወደዱድያኖስ ተመልሶ ሄደ ንጉሡ መኳንንቱን መሣፍንቱንና ሠራዊቱን ሰብስቦ ጣዖት በ ሊያመልክበት አደባባይ ቢያገኘው የ ሚያመልከውና የ ሚያስመልከው ጣዖት ከንቱና የማያድን ሰው ሠራሽ መሆኑን ገልጾ ሰማይንና ምድርን በምድር ላይ ያሉ ፍጥረታትን ሁሉ ለፈጠረ አምላክ መስገድና እሱን ብቻ ማምለክ እንደ ሚገባውም በድፍረት አስተማረው ።

ነገር ግን ንጉሡ ዱድያኖስ እጅግ በጣም ተቆጣ ተናደደ ቅዱስ ጊዮርጊስን አሳሠረው አጋዘው እንዲያሰቃዩትም አዘዛቸው እርሱ ግን የታዘዘበትን ጸዋትወ መከራ ሁሉ በትዕግሥት ለመቀበል በሙሉ ልቡ ቆረጠ ። በእምነቱ ም ጸንቶ በየ አደባባዩ ሁሉ እየተዘዋወረ በድፍረትና በጥብእት መሰከረ አስተማረ ።

በተለይም ልዳ በተባለ ሥፍራ ሄዶ ከንጉሡ ጀምሮ እስከ ተራው ሕዝብ ወርዶ የነበረውን ዶራጎን አርዌ መሣጢ ፊት ለፊት ገጥሞ ቆራርጦ እንደጣለው መጽሐፈ ገድሉ ያረጋግጣል.። ይህ አውሬ ከንጉሡ እስከ ሕዝቡ በውዴታም ይሁን በግዴታ ያመልኩት እንደነበርና ይልቁንም እያንዳንዱ የመጀመሪያ ልጁን ይገብርለት እንደነበር ተጽፎአል ይህ አሰቃቂ አምልኮ በኃያሉ መስተጋድልና ሰማዕት እንደጠፋና በሀገሩ ላይ የክርስትና እምነት እንደተስፋፋበት በመጽሐፈ ገድሉ ተተርኮአል ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ በዚህ ከባድ ተጋድሎ በእሳትና በስለት የተፈጸመበትን ሥቃይና መከራ ተቀብሎ ቢሞትም በፈጣሪው ኃይል ተነሥቶ ማስተማሩን



ቀጠለ ። የቅዱስ ጊዮርጊስን ቅድስና ሲከታተሉ የነበሩት ሦስት መቶ ሰባ ሁለት ሰዎች በክርስቶስ ስም አምነው ተጠመቁ ። ንጉሡም ሰምቶ በሰይፍ ስለት አስፈጃቸው ፤ እነርሱም ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የድል አክሊል ተቀዳጅተዋል ።

ከዚህም ጋር ከዱድያኖስ ሥር የነገሡ ሰባ ነገሥታት የቅ/ጊዮርጊስን ገቢረ ተአምር በተመለከቱ ጊዜ የተቀመጡንባቸውን ወንበሮች አለምልመህ ፤ ብታሳየን ሁላችንም በአንተ አምላክ አምነን እንጠመቃለን ብለው ቃል ገቡ ። ቅ/ጊዮርጊስም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱም ደግሞ ያደርጋል ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል» ያለውን መሠረት በማድረግ ወደ እግዚአብሔር ጸልዮ ወንበሮቻቸውን ሁሉ አለምልሞላቸዋል ነገሥታቱ ግን «የሚጠፉ ከተማ አዋጅ ቢነግሩት አይሰማ» እንዲሉ በክርስቶስ አምነው ለመመለስ አልፈለጉም ። ሌላ ተጨማሪ ተአምር እንድናይ እንፈልጋለንና ሙት አስነሥተህ አሳየን አሉት ። ማቴ - ፲፱-፴፰ እርሱም ከወንዶች ፤ ሴቶችና ከሕጻናት ሙታን መካከል በጸሎቱ አስነሥቶ ቢያሳያቸው ምትሐት ነው አሉት ።

ጠላቶቹ በብረት ምጣድ ጠበሱት ። ወደ ጥልቅ ጉድጓድም ወረወሩት ፤ እርሱ ግን ለሁለተኛ ጊዜ ተነሣ ፤ የማስተማር ሥራውንም ቀጠለ ። ዱድያኖስ ግን ጠበብቱን ጠርቶ እየተከታተሉ እስከ መጨረሻ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ እንዲያሰቃዩት አዘዛቸው ። ወደ ዐውድማ ወስደውም እንደ እህል በበሬ እግር አስጠቀጠቁት ። ሲሞትም ሥጋውን አልሞው ደቂቀ ሰው ይድራስ ወደሚባል ተራራ ወስደው በነፋስ አዘሩት ፤ በተኑት ።

ነገር ግን ወዲያውኑ በቅጠሉ ያረፈው የሥጋውና ያጥንቱ ብናኝ « እኔ ጊዮርጊስ የክርስቶስ አገልጋይ ነኝ ስለ ክርስቶስም እመሰክራለሁ ክርስቶስ ስለ ሰው ልጆች በደል ሞቶ ፤ በሞቱ ሞትን ደምስሶ ለሰው ልጆች ዘለዓለማዊ ነጻነትን ሰጥቶአቸዋል ። ከክርስቶስ በቀር የሚገድል ፤ የሚያድን ሌላ አምላክ የለም» ብሎ ምስክርነቱን አረጋግጦላቸዋል ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሦስት ጊዜ እንደ ሚሞትና እንደ ሚነሣ ከአምላኩ ተነግሮት ነበር ። ይህም ሁሉ ተፈጽሞአል ። ቅ/ጊዮርጊስ የአንዲት መበለት ምሰሶ አለምልሞ እንዲያፈራ አድርጎአል ። የመበለቲቷንም ልጅ ከደዌው ፈውሶታል ፤ የዱድያኖስን ሚስት አሳምኖ ፤ አጥምቆ የሰማዕትነት አክሊል እንድት ቀዳጅ አድርጎአል ። ሰባውን ነገሥታት እሳት አውርዶ አጥፍቶአቸዋል ። በዚህም ተጋድሎ በአገኘው የሰማዕትነት ክብር በስሙ ልጁን የሠየመ ቤ/ክርስቲያንን የሠራ ፤ በስሙ ለተቸገሩ የሰጠ በመንግሥተ ሰማያት እንደ ሚኖር ቃል ኪዳን ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ተቀብሎአል ።

በዚህም ምክንያት ጥር ፲፰ ቀን መታሰቢያው በስሙ በታነጹ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በየ ዓመቱ ከፍ ባለ ስነ ሥርዓት ተከብሮ ይውላል ።በዓሉም ዝርወተ ዓጽሙ በመባል ይታወቃል ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ የፈጸመውን ተጋድሎ ያገኘውን ድልና የሰማዕትነት ክብር ዘወትር በማሰብ በሃይማኖት ምክንያት የ ሚደርሰውን ችግርና ፈተና ሁሉ በትዕግሥት በመቀበል ሰማዕታት ያገኙትን ክብር ለማግኘት መጣር እንደሚገባ ገድሉ ያስተምረናል ።

ሊቀ ትጉሃን ገ/ክርስቶስ ኃ/ ማርያም

# አስተርእዮ

አስተርእዮ የሚለው ቃል በጽርዕ (ግሪክ) ቋንቋ ኤጲፋኒ ይባላል ። መገለጥ ፡ መታየት ፣ በሰው ፊት እየተመላለሱ ማስተማር ማለት ነው ። ከልደተ ክርስቶስ ዋዜማ ጀምሮ እስከ ዓቢይ ጾም ድረስ ባሉት ቀኖች ተወልደ አንሶሰወ ፤ አስተርእየ ፣ ተጠምቀ ፣ ወዘተ የሚሉ ቃላት በብዛት ይነገራሉ ፣ በቅዱስ ወንጌል የሚነበቡት ምንባቦች የሚሰበኩት ስብከቶች ፣ የሚዘመሩት መዝሙሮች ሁሉ እነዚህን የተጠቀሱትን በጉልህ የሚገልጹ ናቸው ።

እግዚአብሔር አምላክ ዓለምን ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ከመፍጠሩ አስቀድሞ የነበረ አሁንም ያለ ወደፊትም ይህን ዓለም አሳልፎ ለዘለዓለም የሚኖር መሆኑን እናምናለን ፤ እግዚአብሔር ከፍጥረተ ዓለም ጀምሮ መገለጫ ያደረገው ሰውን ነው ። ይህንንም “ ንግበር ሰብአ በአርአያነ ፣ ወበአምሳሊነ” ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር በሚለው ቃል ለመረዳት ይቻላል ፤ ዘፍ ፣ ፩ ፡ ፳፮ ። ይሁን እንጂ በቃል ከመነገር በስተቀር በግልጽ ሰው ሆኖ እንደሰው የታየበትና የተመላለሰበት ጊዜ አልነበረም ነቢዩ ሙሴ ከባለሟልነቱ የተነሣ በባህርይህ ሁነህ ልይህ ብሎ ቢለምነው ፊቱን ዓይቶ ለአንዲት ሰዓት እንኳን በሕይወት ለመቆየት የሚችል የለም ብሎታል ዘፀ ፡ ፴፫ ፡ ፲፯—፳፫ ኋላም ወንጌላዊው ዮሐንስ” እግዚአብሔርን በባህርዩ ያየው የለም ብሏል ። ዮሐ ፩ ፣ ፲፰ ።

አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በማፍረሳቸው በመከራ ዓዘቅት ውስጥ ወድቀው ሲሠቃዩ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሰው ሁኖ ሥጋ ለብሶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ እየተመላለሰ አስተምሮ ፣ ተሰቅሎ ፤ ሙቶ ፣ ተነሥቶ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ እንደሚያድናቸው ተስፋ ሰጣቸው ፤ የሰጣቸውም ተስፋ ዕለቱን አልተፈጸመም ፤ በትንቢት እየተነገረ በሱባኤ እየተቆጠረ በምሳሌም እየመተሰለ በመነገር ብዙ ዘመን ኑሯል ።



www.ethiopianorthodox.org

ስለ ክርስቶስ በሥጋ መገለጽ ብዙ ነቢያት ትንቢት ተናግረዋል ፤ ሱባኤም ቆጥረዋል ፤ ምሳሌም እየመሰሉ ተናግረዋል ። የተነገረው ትንቢት ሲፈጸም ጌታችን ከድንግል ማርያም በግብረ መንፈስ ቅዱስ ተጸንሶ ተወለደ ። ከተወለደም በኋላ አምላክነኝ ብሎ ዕለቱን አላደገም ፣ እንደ ሕፃናት ቀስ በቀስ አደገ እንጂ የዕብራውያንንም ሕግና ሥርዓት አላፋለሰም ፤ በተወለደ በስምንት ቀን ወደ ቤተ ግዝረት ገብቶ የግዝረት ሥርዓት ተፈጽሞለታል ። ስሙም ኢየሱስ ተብሎ ተሰይሞአል ። በዓርባ ቀን ደግሞ ዕጕለ ርግብ ዘውገ ማዕነቅ ይዘው ወደ ቤተ እግዚአብሔር ወስደውታል ፣ በዓመትም ሦስት ጊዜያት ወደ ቤተ መቅደስ እየወሰዱ እጅ ያስነሡት ነበር ።

ይህ ሁሉ የሚያስረዳው ሁሉን ለማድረግ የማይሳነው አምላክ ሲሆን በኃይሉ በሥልጣኑ ሳይመካ የሰውን ሥርዓት ሳያፋልስ ጠብቆ ቀስ በቀስ ማደጉን ነው ፤ ክርስቶስ ከኃጢአት በስተቀር ያልተሳተፈበት ማኅበራዊ ኑሮ አይገኝም ። ምንም በልዩ ልዩ መንገድ ከማስተማር ባያርፍም አስራ ሁለቱን ሐዋርያት ሰባ ሁለቱን አርድእት፣ ሠላሳ ስድስቱን ቅዱሳት አንስት መርጦ በዚህ ዓለም እየተመላለሰ ተአምራትም እያደረገ በሰፊው ያስተማረው በዮሐንስ በፈለገ ዮርዳኖስ ከተጠመቀ በኋላ ነው ። በኢየሩሳሌም አካባቢ በገሊላ በናዝሬት በይሁዳና በመሳሰሉትም ቦታዎች በግልጽ ሲያስተምር የዕውራንን ዓይን አብርቷል ። ለምጻሞችን አንጽቷል ፣ ደንቆሮዎች እንዲሰሙ ዲዳዎች እንዲናገሩ አድርጓል ። እነዚህን የመሳሰሉ ተአምራትን እያደረገ ያስተማረባቸው ቀናት ተጠቃለው ዘመነ አስተርእዮ (ኤጲፋኒ) ተብሎ ተሠይሞአል ፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር አስተምሯል ። ከባሕርይ አባቱ ተልኮ የመጣበትን ተግባር ካከናወነ በኋላ በመልዕልተ መስቀል ላይ ተሰቅሎ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ በመንጸፈ ደይን ወድቆ በእግረ አጋንንት ሲጠቀጠቅ የኖረውን የሰው ወገን ሁሉ አድኖታል ፤ በእርሱ ስም አምነን የተጠመቅን ሁሉ አሁን ድኅነትን አግኝተናል ፤ ስለዚህ በጥምቀት ከሥላሴ ያገኘነውን የልጅነት ክብር ጠብቀን ተጠንቅቀን መኖር ይገባናል ።

## አስተርእዮ ማርያም

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ያረፈችበት ጥር ሃያ አንድ ቀን አስተርእዮ ማርያም ይባላል እመቤታችን በዚህ ዓለም የኖረችው ፷፬ ዓመት ነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከዓረገ በኋላ ወደ ጎልጎታ እየሄደች ከጌታ መቃብር ትጸልይ ነበር ። ወደ እርሷ መጥቶ ከዚህ ዓለም በሞት እንደምትለይ ቢነግራት ዮሐንስ ወንጌላዊን በሕይወት ያሉትንና የሞቱትን ሐዋርያት እንዲያመጣለት ለመነችው ። ወዲያውኑ ሁሉንም ሰብስቦ አመጣላት ። እመቤታችንም «የለመንኩህን ሁሉ ስለፈጸምክልኝ አመሰግንሃለሁ” ብላ ልጅዋን ወዳጅዋን ኢየሱስ ክርስቶስን አመሰገነችው ። ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል » በማለት ጸሎቷን ስትፈጽም ጌታችን እልፍ አዕላፋት መላእክትን አስከትሎ መጣና ዕረፍቷንና ያዘጋጀላትን ክብር ነገራት በዚያን ጊዜም እጅግ በጣም አስደናቂ የሆኑ ተአምራት ተፈጽመዋል ፣ ዕውራን አይተዋል ፣ ለሞጻሞች ከለምጻቸው ነጽተዋል ፣ አንካሶችና ሽባዎች እየተነሡ ሩጠዋል ፤ ዲዳዎች እንደበታቸው ተፈትቶላቸው መናገር ችለዋል ። አጋንንትም እየጮሁ ከበሽተኞች ወጥተዋል ፤ እንዲሁም በልዩ ልዩ ደዌ የተለከፉት ሕሙማን ሁሉ እመቤታችን ወደ አለችበት ሲቀርቡ ከያዛቸው ደዌ ተፈውሰዋል ።

እመቤታችን “ልጄ ወዳጄ ሆይ ! በአንተ ስም አምነው በእኔ የተማፀኑትን ልመናቸውን ተቀብለህ ዋጋቸውን ስጣቸው ፣ የ ሚያቀርቡትንም መብዓ ሁሉ ተቀብለህ ቤታቸውን ባርክላቸው” ስትል ለመነችው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም“ የለመንሽውን ሁሉ እፈጽምልሻለሁና ደስ ይበልሽ” አላት በዚያ ጊዜ ሐዋርያት እያለቀሱ ወደ እመቤታችን ቀርበው እንድትባርካቸው ለመኗት ፣ እመቤታችንም ባርካቸው ስታበቃ ቅድስት ነፍሷ ከቅዱስ ሥጋዋ ተለየች ! ሐዋርያት ሊቀ ብሩ ወደ ጌቴሴማኒ ይዘዋት ሲሄዱ አይሁድ ለምቀኝነት አያርፉምና ቀድሞ ልጅዋን ጠልተን ተመቅኝተን ገርፈን ሰቅለን ብንገድለው ደቀ መዛሙርቱ እንደገና ተነሣ ዓረገ ሁለተኛም ዓለሙን ለማሳለፍ ይመጣል እያሉ በማስተማር ሲያውኩን ይኖራሉ ፤ አሁን ደግሞ ይህችን ተነሣች ዓረገች እያሉ ሲያውኩን ሊኖሩ አይደለምን ? ስለዚህ በድኗን በእሳት ማቃጠል አለብን ብለው ተሰብስበው ሄዱና ከመካከላቸው አንዱ አይሁዳዊ ተራምዶ የአልጋውን ሸንኮር በእጆቹ ያዘው መልአኩ በሰይፍ ሁለት እጆቹን ቀነጠሳቸውና ከአጐበሩ ላይ ተንጠልጥለው ቀሩ ወዲያው በክርስቶስ ስም አምኖ በእመቤታችን ስለተማፀነ የተቆረጡት እጆቹ እንደ ነበሩ ተመልሰውለታል ፣ በዚያን ጊዜ ሐዋርያት ደንግጠው በየፊናቸው ሲበታተኑ እመቤታችንን ከዮሐንስ ወንጌላዊ ጋር በደመና ነጥቆ ወስዶ በገነት በዕፀ ሕይወት ሥር አስቀመጣት ፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዮሐንስ ሂዶ በገነት መኖሯን ለሐዋርያት ነገራቸው ፤ እነርሱም ዮሐንስ አይቶ እኛ ሳናይ በማለት ነሐሴ አንድ ቀን ሱባኤ ገብተው ሲጾሙ ሲጸልዩ በአሥራ አራተኛው ቀን የእመቤታችንን ሥጋ አምጥቶ ሰጥቷቸው ቀብረውታል ። በሦስተኛውም ቀን ተነሥታ ሐዋርያት እያዩአት ዓርጋለች ።

እመቤታችን ጥር ፳፩ ቀን ያረፈችበት ሲሆን ከተቀበረች በኋላ በሦስተኛው ቀን ተነሥታ ያረገችው ነሐሴ ፲፮ ቀን ነው « ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር » የሚባለውም ስለዚህ ነው ።

ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ በዛብኅ




## «ዴር ሡልጣን የእኛ ነው» ! !

ኢትዮጵያ በመካከለኛው ምሥራቅ ከሚገኙት ጥንታውያን የሃይማኖትና የታሪክ አህጉር መካከል አንደኛዋ መሆንዋ በቅዱሳት መጻሕፍትና በታሪክ ሠነዶች የታወቀ ነው ።

በብሉይ ኪዳን የታሪክ ክፍል በመጽሐፈ ነገሥት ኢትዮጵያ የኢየሩሳሌም ወሰንተኛ እንደ ነበረች ተመዝግቧል ። (ነገሥት ካልዕ ፲፱ ፡ ፬ ፡ ዜና መዋዕል ካልዕ ፡ ፲፩ ፡ ፱ ።)

“ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች” ተብሎ በነቢዩ እግዚአብሔር ዳዊት የተነገረውም ኢትዮጵያ በአንድ አምላክ የምታምን ሀገር መሆኗን የ ሚያሳይ ግልጥና ዛሬም በአስረጅነት የ ሚታይ ጉልህ ማስረጃ ነው ።

መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠራቸው ቦታዎች ከእምነት ጋር በተያያዘ ሁኔታ የታወቁትን ሀገሮችና ሕዝብ ነው እንጂ በስፋትና በብልጽግና አይደለም ።



በኢየሩሳሌም ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት

ኢትዮጵያውያን መሥዋዕትን ለአምላካቸው ለእግዚአብሔር ለማቅረብና ጥበበ እግዚአብሔርንም ለመረዳት በየጊዜው ኢየሩሳሌም ይሄዱ እንደ ነበር በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቦ ይገኛል ።

ቀደም ሲል በብሉይ ኪዳን ፣ በኋላም በሐዲስ ኪዳን እምነትና ሥርዓት መሠረት ኢትዮጵያውያን በየጊዜው ወደ ኢየሩሳሌም እየሄዱ ሥርዓተ አምልኮታቸውን በሚፈጽሙበት ወቅት በኢየሩሳሌም ማረፊያ ቦታ እንደ ነበራቸው በታሪክ የተረጋገጠ ነው ።

ይህም ቦታ በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የታወቀችው ኢትዮጵያዊቷ ንግሥተ ሳባ ከልደተ ክርስቶስ በፊት በ፱፻፹ ዓመት አካባቢ ጥበበ እግዚአብሔርን ለመረዳት ፣ ኢየሩሳሌምን ለመጎብኘትና እምልኮተ እግዚአብሔርን ለመፈጸም ወደ ኢየሩሳሌም ሔዳ በነበረበት ወቅት ንጉሥ ሰሎሞን በኢየሩሳሌም ከተማ ማረፊያ ቦታ እንደሰጣት በኢትዮጵያ ታሪክ ነገሥት ተመዝግቦ ይገኛል ። ይህም ቦታ በታሪክ “ዴር ሡልጣን” በመባል የታወቀ ነው ። ዴር ሡልጣን ማለትም የመንግሥት ገዳም ማለት መሆኑ ታውቆአል ።

እግዚአብሔር አምላክ በነቢዩ በሶፎንያስ እንደበት “ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የ ሚማልዱኝ (የሚለምኑኝ) የተበተኑት ልጆቼ ቍርባኔን ያመጡልኛል” ሲል በተናገረው መሠረት ኢትዮጵያውያን ከጥንት ጀምሮ መሥዋዕታቸውንና ቍርባናቸውን ለእግዚአብሔር የ ሚያቀርቡት በማዕከለ ምድር ዴር ሡልጣን (ሶፎ ፡ ፫ ፡ ፲ ፡) ተገኝተው ነው ።

በነቢዩ እግዚአብሔር ዳዊት “ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር” ተብሎ የተነገረው ትንቢት ፡ በንግሥተ ሳባ በኋላም በሕንደኬ ንግሥት



www.ethiopianorthodox.org

መልእክተኛ ጃንደረባ መጠመቅና የክርስትናን እምነት ይዞ ወደ ሀገሩ ኢትዮጵያ መመለስ ትንቢቱ መፈጸሙን ያስገነዝበናል ።

ከልደተ ክርስቶስ ወዲህ ካራተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያውያን መናንያን የጥንት ይዞታቸው (ዓጽመ ርስታቸው) በሆነው ቦታ ማለት በዴር ሡልጣን ገዳም መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን እየፈጸሙ ይኖሩ ነበር ። በየዘመኑ የተነሡት የኢትዮጵያ ነገሥታት በሀሳብም በተግባርም ከዚህ ገዳም ያልተለዩ ነበሩ ።

ለምሳሌ ፣ በ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩት ዓፄ ዘርዐ ያዕቆብ በዴር ሡልጣን ገዳማችን ለሚኖሩት መነኮሳት በየጊዜው የሰላምታና የማጽናኛ ደብዳቤ ይጽፉላቸው እንደ ነበርና ፣ ለምግባቸውና ለልብሳቸው የሚሆናቸውም በየሁለት ዓመቱ አንድ መቶ ሕልቀ ወርቅ ማለት የወርቅ ወቄት ይልኩላቸው እንደ ነበር በታሪክ ተመዝግቧል ። ይህም በየሁለት ዓመቱ የማያቋርጥ ሥሪት እንዲሆንላቸው መወሰናቸው በታሪኩ ተመልክቷል ።

ከዚያም በይቀጥላል በየጊዜው የተነሡ የኢትዮጵያ ነገሥታት እነ ዓፄ ዮሐንስ ፣ እነ ዓፄ ምኒልክ ፣ እነ እቴጌ ጣይቱ ፣ እነ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ፣ እነ አጼ ኃይለ ሥላሴ ፣ እነ እቴጌ መነንና ሌሎችም ደጋግ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች በኢየሩሳሌም ለሚገኘው ለዴር ሡልጣን ገዳምና ለሌሎቹም ኢትዮጵያውያን ገዳማት በየጊዜው አስፈላጊውን ርዳታ አድርገዋል ።

ከዚህ በላይ ባጭሩ የተገለፀው "ዴር ሡልጣን" ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዐፅመ ርስት ገዳም መሆኑን ያረጋግጣል ።

እውነተኛው ታሪክ ይህ ሆኖ ሳለ እ - አ - ዘ - አ - በ፱/፰/ ፲፱፻፺፫ ዓ/ም በዐረብኛ ቋንቋ ታትሞ የወጣው "እልኩድስ" የተባለው ጋዜጣ ይህን የታሪክ ሐቅ ባለመገንዘቡና ሳያጠና ዴር ሡልጣን የኮፕት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ይዞታ ነው ብሎ የጻፈው በታሪክ ያልተደገፈ ከዕውነት የራቀ መሠረተ ቢስ ዘገባ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ።

በኢየሩሳሌም ዴር ሡልጣን ገዳም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ንብረት መሆኑን አውቀው ምስክርነታቸውን በጽሑፍ ያረጋገጡ ብዙዎች ናቸው ። መረጃዎቹም በእጃችን ይገኛሉ ።

ስለዚህ እውነተኛውን ታሪክ በሐሰት ለመለወጥ የታጣው "እልኩድስ" የተባለው ጋዜጣ የዴር ሡልጣን ገዳም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ንብረት መሆኑን አውቆና ተረድቶ ስህተቱን ባስቸኳይ እንዲያርም ጥሪያችንን እናስተላልፋለን ።

«ዴር ሡልጣን የኛ ነው» ! !
"ወስብሐት ለእግዚአብሔር"

---

## የጋዜጦችና መጽሔቶች መልእክት ለሰላም

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጽኑ መሠረት ላይ የታነጸች ጥንታዊት ፣ ብሔራዊትና ሐዋርያዊት ስለሆነች ፣

በጽኑ ሃይማኖታቸውና በተወደደ ሥነ ምግባራቸው ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው የቀረበና የሠመረ ግንኙነት እጆቻቸውን ወደ እግዚአብሔር ዘርግተው ቀን ከሌሊት በመማለድ ሀገሪቱን ሀገረ እግዚአብሔር ሕዝቡን ሕዝበ እግዚአብሔር አሰኝተው በቅድስና አስጠርተውት የኖሩባት የሊቃውንትና ደጋግ ሰዎች መገኛ ናት ።

ዛሬም ለሃይማኖትና ሥነ ምግባር መጠበቅ ፣ ለሀገርና ታሪክ መከበር ፣ ለትውልድ ነፃነትና ደኅንነት ፣ ለዓለም ሰላምና ብልጽግና የ ሚጸልዩ ምስክርና ጥበብ ያልጎደላቸው ደጋግ አበው የ ሚገኙባት ፣ የገቢረ ተአምራትና የትምህርተ መለኮት ፀጋ ያልተጓደለባት ስለሆነች ቤተ ክርስቲያናችን መሠረቷ አሁንም የጸና ነው ።

ምን ጊዜም በጉዞ ላይ እንቅፋት ፣ በበጎ ሥራ ላይ ፈተና ይኖራል ።

" - - ወዳጆች ሆይ ፣ በእናንተ መካከል
እንደእሳት ሊፈትናችሁ ስለሚሆነው
መከራ ድንቅ ነገር እንደመጣባችሁ
አትደነቁ ፤ - - ክብሩ ሲገለጥ ሐሤት
እያደረጋችሁ ደስ እንዲላችሁ ፣ በክርስቶስ
መከራ በምትካፈሉበት ልክ ደስ ይበላችሁ ፤
ስለክርስቶስ ስም ብትነቀፉ የክብር መን
ፈስ ፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ በናንተ
ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ" ተብሎ

እንደተጻፈ ቤተ ክርስቲያን ያለ ችግርና ፈተና ከዚህ ደርሳለች ማለት አይቻልም ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሠረቷ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ በየዘመኑ የተነሳው ነፋስ ፣ የፈሰሰው ጎርፍና ማዕበል ሁሉ ከመሠረቷ አላናወጻትም ። ወደፊትም ሊያናውጻት አይችልም ። በኢየሱስ ክርስቶስ መሠረትነት ፣ በሊቃውንት እዕማድነት የተደራጀ የብዙ ሚሊዮን ሕዝበ ክርስቲያን ባለቤት ስለሆነች ማንኛውም ኃይል ከመሠረቷ ሊያናውጻትና ሊያነቃንቃት አልቻለም ።



በአሁኑ ጊዜ በዲሞክራሲ ስም በየዕለቱ እየታተሙ ከሚበተኑት ጋዜጦችና መጽሔቶች አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ አቋም የሚያናጋ የአበውን ክብርና ቅድስና የሚያጎድፍ ፣ ሥርዓተ ቀኖናዋን የሚነቅፍ ዜና ሲያስተጋቡ እየተስተዋለ ነው ። በውስጥ እስተዳደሩዋ በመግባት በአበውና ምእመናን መካከል የቆየውንና ያለውን አንድነት የሚለያይ እመለካከትን የሚከፋፍልና የጥላቻን መንፈስ የ ሚዘራ ፍሬ አልባ ወሬ ሲያቀርቡም በትዝብት እየታየ ነው ። ቤተ ክርስቲያን ሁሉንም በትዕግሥትና በጽሞና ስትመለከተው ቆይታለች ። እስከ መጨረሻውም ተንዘብ አድርጋ የምትጓዘው ትዕግሥትን ነው ።

ሁሉም ጋዜጦችና መጽሔቶች ከዜና ጀምሮ ሕዝቡ የዓለምንና የአካባቢውን የዕለት ከዕለት ሁኔታ እየተከታተሉ በመጻፍና በማስንበብ ፣ የዕውቀት አድማሱን እንዲያሠፉ ፣ ስለማኅበረ ሰብ ጉዳዮች ትንታኔና ግንዛቤ እንዲያገኝ ቢያደርጉ ለሀገር ሰላም ለወገን ፍቅርና ልማት የሚያበረታታ ገንቢ ትምህርት ቢሰጡ እጅግ ባማረና በተወደደ ቤተ ክርስቲያንም የሣቡ ደጋፊ ፣ የሥራው ተባባሪ በሆነች ነበር ። በተቃራኒው ግን የብዙ ሚሊዮን ሕዝበ ክርስቲያን አንድነት ፣ የብዙ ሊቃውንትና ደጋግ አበው የቅድስና ቤት የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና አሠራር ለማናጋት መሠረት በሌለው የአሉባልታ ቅብብሎሽ ፍሬ ቢስ ክስና ስሞታ ማስተጋባት ቤተ ክርስቲያንን ብቻ ሳይሆን ተመልካችንም ያሳዝናል ።

በተለይ "ቢላል" የተባለው የእስልምና መጽሔት

— በክርስትና እምነትና በቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቀኖና ፣

— በሃይማኖት ሊቃውንት ትምህርትና እምነት ፣

— በቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉምና ይዘት ደጋግሞ

ያሠፈረው ጽሑፍ ፣ ሕዝበ ክርስቲያንን የሚያስቆጣ ለጠብና ግጭት የ ሚያነሳሳ በመሆኑ በትዕግስትና በዝምታ ብቻ የሚታለፍ አልሆነም ።

ስለዚህ በልዩ ልዩ መጠሪያና አርእስት የሚታተሙ ጋዜጦችና መጽሔቶች ከነቀፋና ስሞታ ይልቅ፣ ለሰላምና ለአንድነት ፣ ለልማትና ለዕድገት ፣ ለዕውቀትና ለምርምር በሚረዱ ገንቢ አስተያየቶች ላይ ብዕራቸውን ቢያመቻቹ የተሻለ መሆኑን በማስገንዘብ፣ ቤተ ክርስቲያን ምክሯንና በጎ መልእክቷን ታስተላልፋለች ።

የቢላል መጽሔት በየወቅቱ ላሠፈራቸው ጊዜ ወለድ የአክራሪነት ጠባይ ያላቸው ጽሑፎች ግን ቅ/ሲኖዶስ በስፋት ተወያይቶ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥቷል ።

<u>ቢላል !</u> የእስልምና መጽሔት ቁጥር ፫ በኅዳር ወር ፲፱፻፹፭ ዓ/ም ባወጣው እትሙ ላይ በገጾቹ በተለይም በአክሱም የክርስትና እምነት ተከታዮችና የእስልምና አማኞች መካከል የደረሰው ግጭት መንሥኤ ምንድነው ? በ ሚል መጠይቅ መነሻ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ለሰጡት መግለጫ ከእውነት የራቀና የተዛባ ትርጉም በመስጠት ለመተቸት ሞክሯል ።

በመሠረቱ ቅዱስነታቸው የሰጡት መግለጫ "ሃይማኖትና ታሪክ እንዲጠበቁ ፣ ይዞታ በባለ ይዞታው እንዲከበር የ ሚያመለክት እንጂ የማንንም እምነትና መብት የ ሚነካ አይደለም ።

አክሱምም በክርስትና ማእከልነትዋ ዓለም የሚያውቃት እንደመሆንዋ መጠን "የአክሱም ይዞታ የክርስቲያኖች ይዞታ ነው" ማለት አድሏዊነት አለመሆኑ በሁሉም ዘንድ ግልጽ ሲሆን የኢትዮጵያውያንም እምነት ነው ። አሌ የማይባለው የታሪክ እውነትም ይኸው ነው ። ይህም በረዥም ዘመን የታሪካችን ጉዞ በቀደምት ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ብዙ ውጣ ውረድ የተደረገበትና እልባት አግኝቶ ተጠብቆ የኖረ ነው ።

ክርስትናና እስልምና በአንድ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ አስመስሎ መናገርም ታሪክን በትክክል አለመረዳትና ሐቅን ለመሸፈን መሞከር ነው ።

መጽሔቱ እንዳሰፈረው "ዜጎቹን በሃይማኖት ከፋፍሎ ለጥፋት መጋበዝና በሀገሪቱ ላይ የሥጋት ደመና እንዲያንዣብብ ማድረግ" ይሏል ይኸው ነው ።

ክርስትናና እስልምና ወደ ኢትዮጵያ በመግባት መቀዳደም ብቻ ሳይሆን በአመሠራረታቸውም በመካከላቸው ያለው የዘመናት ርቀት ሲታይ ፈጽሞ የማይገናኝ ነው ። ይኸውም ክርስትና ከእስልምና የ፮፻ ዘመን ቅድምና አለው ።

ኢትዮጵያን የሚያምኑባት ፤ ዓለም የሚያውቀው ከክርስትናው እምነት በፊት አክሱም ለክርስትና እምነት መሠረት ለሆነው ለብሉይ ኪዳን ማዕከል መሆንዋን ነው ። የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርካችን መግለጫም ከዚህ ውጭ እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል ።



www.ethiopianorthodox.org

ትናንትም ሆነ ዛሬ የቤተ ክርስቲያናችን መልእክትና ዓላማ ምኞትና ጸሎት በሃይማኖት ልዩነት ሳይኖር መላው ኅብረተ ሰብ በፍቅር ፣ በሰላምና በአንድነት እንዲኖር ነው ።

ይኸው የእስልምና መጽሔት በአንደኛ ዓመት ቁጥር ፲ ፣ ፲፱፻፹፭ ዓ/ም እትሙ «ኢየሱስ ነቢይ ወይስ ጌታ » በሚል መነሻ የመላውን ዓለም የክርስትና እምነት የሚያናጋና የክርስትና እምነት ተከታዮችን ሁሉ በቁጣ የሚያነሣሣ የዘለፋ ቃል አስፍሯል ። መጽሔቱ እንዳለው ሳይሆን በክርስትና እምነት መሐመድ የመጀመሪያም የመጨረሻም ነቢይ አይደለም ። በክርስትናውም ዓለም በነቢያት አይታወቅም በክርስትና እምነት መሐመድ ከክርስቶስ ጋር አይወዳደርም ። ትምህርታቸውም ሆነ መልእክታቸው አይነፃፀርም ። ክርስቶስ አምላክ ነው ። መሐመድ ግን ፍጡር ነው ። ስለዚህ ፍጡርና ፈጣሪ አይወዳደሩም ።

መጽሔቱ "ዛሬ በእውነት ጉዳይ ስንነጋገር ነቢያት የተውልንን ቅዱሳት መጻሕፍት በእጃችን ይዘን ነው ። ከዚህም ጋር በተጨማሪ የታሪክ ድርሳናትን ፈትሸን ፣ መርምረንና ተመራምረን ለእምነታችን ትክክለኛነት ያልተድበሰበሰ ማስረጃ ለማቅረብ እንችላለን ። - - እውነታው ይህ ሁኖ ሳለ ፩ሺ፬፻ ዓመታት ወደ ኋላ ተመልሶ ነቢይን ለመዝለፍ መሞከር ድንቁርና እንጂ ሌላ አንዳችም ስም ሊሰጠው አይችልም" ብሏል ።

፱ኛ ግንዛቤ አለማወቅ የምንለው ፈጣሪንና ፍጡርን አለመለየት ነው ። ወደ ኋላ ፩ሺ፬፻ ዘመን ተመልሶ አዲስ የእምነት መሠረት ለመጣል መሞከር ማለትም ይህ ነው ።

ይኸው ጽሑፍ ሙስሊሞች ኢየሱስን ታላቅና ክቡር የፈጣሪ መልእክተኛ መሆኑን በፍጹም ልባቸው እንደሚያምኑና እንደ ሚቀበሉ ያትታል ። በክርስትናው እምነት ግን ኢየሱስ ክርስቶስ የነቢያት ፈጣሪ፣ አምላክ ወልደ አምላክ ፣ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በተዋሕዶ የሚታመንና የሚሰገድለት የባሕርይ አምላክ ነው እንጂ እንደ ቢላል መጽሔት አባባል ፍጡር አይደለም ።

ምሥጢረ ሥላሴንም በተመለከተ መጽሔቱ በማያውቀውና ከእስልምና እምነት ጋር ግንኙነት በሌለው ትምህርት በመግባት ለማተት ሞክሯል ።

በመሠረቱ እስልምና ከክርስትና የ ሚለይበት ዋናው ምክንያት የአብ ፤ የወልድ ፤ የመንፈስ ቅዱስን አንድነትና ሦስትነት አለመረዳቱና አለማመኑ ነው ።

«ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ብሥራት በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከንጽሕት ፤ ቅድስት ድንግል ማርያም መጸነሱንና መወለዱን እንቀበላለን» እያሉ በሌላ በኩል «ኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል ። » በማለት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል የተናገረውን መካድ የሚያመለክተው የጸሐፊውን ሐሳብ መ[illegible] የአመለካከት ጉድለት እንጂ ቅዱሳት መጻሕፍት በትምህርታቸው ነው ግጭት የለባቸውም ። የክርስቲያኖችም እምነት ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት የወጣ አይደለም ።

ይህን አባባል ማንም ሰው በግልጽ ሊመለከተው እንደ ሚችል በአንድ በኩል «ኢየሱስ ክርስቶስ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ብሥራት ድንግሊ ዓለም ከድንግል ማርያም ያለ አባት መወለዱን በአምላክነቱ ብዙ ገቢረ ተአምራት መፈጸሙን ፤ ወደ ሰማይ ማረጉንና ዳግመኛ ወደ ዓለም መምጣቱን እየተቀበሉ በሌላ በኩል ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ በመልአኩ እንደተገለጸው ለሥርየተ ኃጢአትና ለዓለም መድኃኒትነት መሆኑን መካድ ፤ ከዚያም አልፎ «በምሁራንና ሊቃውንት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ምንነት በተደረገው ጥናትና ምርምር የተደረሰበት ማጠቃለያ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ስለመጋጨቱ እንጂ በቁርዓን ላይ ከሰፈረው እስላማዊ አመለካከት ጋር በእጅጉ አለመጣጣሙ ነው» ብሎ ሐተታ ማሳለፍ እርስ በርስ የ ሚጋጭ አሳብ ነው ማለት ይኸ ነው ።

መጽሐፍ ቅዱስና ቁርዓን በ ሚያስተላልፉት መልእክትም ሆነ በ ሚሰጡት ትምህርት ግንኙነት የላቸውም ። የ ሚታረቁበትና የ ሚጣጣሙበት መንገድ የለም በቁርዓን ውስጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ አንዳንድ ቃላትና የ ሚጠቃቀሱ ፀረፍተ ነገሮች ቢኖሩም ክርስትናውና መጽሐፍ ቅዱስ ከእስልምናውና ከቁርዓኑ መቅደማቸውን የ ሚያመለከት እንጂ የሁለቱን አንድነት አያመለክትም ።

ቢላል እንዳለው «በእግዚአብሔር መንፈስ በተጻፉ በመለኮታዊ መጻሕፍት ማመን ከእምነት ዓምዶቻቸው አንዱ መሆኑን ካወቁ ፤ የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃላቸውንና ትርጉማቸውን ፤ በትክክል እየተረዱ የእምነትን አቋም ማስተካከል ተገቢ ነው ። ጸሐፊው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ እውነቶች መኖራቸውንና ምሥጢራቸውንም ከክርስቲያኖች በተሻለ ሁኔታ የ ሚረዱት መሆኑን ጠቅሶ ያቀረበው የመጽሐፍ ቅዱስጥልቅ ግንዛቤ ያለው መስሎ ለመታየት ከማሰቡ በቀር ጽሑፉ እርስ በርሱ የተጋጨ ነው ።

የቢላል ጸሐፊ ፤ ከሔርማን መጽሐፍ ያለውን ቀንጭቦ «ከሁሉም በፊት አምላክ እንደሆነ ሁኑንም ነገር እንደፈጠረና ሥርዓት እንዳስያዘ ከምንም አስቀድሞ ከነበረ ፤ ነገሮች እንዲሆኑና እንዲፈጠሩ ማድረጉን ፣ እርሱም ሁሉን ያቀፈና ፤ ግን እርሱን የሚያቅፍ ምንም ነገር እንደሌለ እመን» የሚለውን ለአንድነትና ለሦስትነት መቃወሚያ አድርጎ ለማሳየት ሞክሮዋል ። ይህ የሔሮማን ቃል የ ሚደገፍ ፤ በክርስትና እምነትም የሚታመን ነው ።



ይሁን እንጂ የቢላል ጸሐፊ ከሔርማን መጽሐፍ በሚገባ የሚተዋወቁ መስሎ አይታይም ። ምክንያቱም በዚሁ መጽሐፍ በአምሳል ፱ በክፍል ፲፪ «አንተ ልብ የሌለህ ሰነፍ ሰማ አስተውልም ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍጥረተ ዓለም አስቀድሞ ነበረ ። - - - - - በመጨረሻውም ዘመን ተገለጠ - - - በ ሚወደው ፣ በ ሚወልደው በአንድ ልጁ ስም ካልሆነ በስተቀር ማንም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት አይችልም ። - - - - በእግዚአብሔር አብ በእግዚአብሔር ወልድ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የ ሚያምኑ ሁሉ በመንፈስና በሁለንታዊ ሕይወታቸው አንድ ናቸው ይላል ። የሔርማንን መጽሐፍ በማስረጃነት የ ሚቀበል ከሆነ ለእስልምና ቦታ የለውም ማለት ነው ።

የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ከተለያዩ ሕዝቦች ባህልና የአንዋወር ሥርዓት ጋር እየተዛመደ ፤ በይበልጥም ከግሪክ ቋንቋና ፍልስፍና ጋር እየተቀየጠ በመምጣቱ ኢየሱስን ከነቢይነት ወደ አምላክነት እንዲሸጋገር ኋላም የሥላሴን ትምህርት እንዲጀመር ሆነ «ተብሎ በቢላል - - - የተመለከተው በስሜት የተጻፈ እንጂ ከመሠረታዊው የሃይማኖት ትምህርት ጋር ዝምድና የለውም ። በቅዱሳት መጻሕፍትም የተደገፈ አይደለም ።

ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ ሃይማኖቱ የቀና ፤ መፍቀሬ እግዚአብሔር ነው ። የተቀደሰ ታሪኩን እሉባልታ አይለውጠውም ። ከአለማመን ወደ ማመን መለወጥም አረመኔ አያሰኝም ። አረማዊነት ይልቅ በእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት አለማመን ነው ።

መጽሐፍ ቅዱስን እናውቃለን ከተባለ ፤ የመጽፍ ቅዱስ መልእክትም ትምህርትም ይህ ነው ። «ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም» ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በ ሚታመን ሁሉ እግዚአብሔር በርሱ ይኖራል ፤ እርሱም በእግዚአብሔር ይኖራል» (፩ ፣ ዮሐ ፣ ፬ ፣ ፫ ፣ ፲፭) ማቴ ፳፰ ፣ ፲፱) ።

የቢላል ጸሐፊ አሁንም ሐተታውን በዚሁ ጉዳይ ላይ በማራዘም ከ፫፻፳፭ ዓ/ም የኒቅያ ጉባኤ ጀምሮ በየዐረፍተ ዘመኑ የተካሄዱትን የሃይማኖት ጉባኤያትና ውሳኔዎች ለማጥላላትና ትክክለኛውን የክርስትና እምነት አበጥረው ያስተማሩትን እነ ቅዱስ አትናቴዎስን የመሰሉትን ሊቃውንት በመናፍቅነት ከተወገዙትና ከተለዩት ከነ አርዮስ በማጫፈር የተምታታ ታሪክ ተርኳል ።

ስለ ምሥጢረ ሥላሴ ባስተማረው ትምህርተ ሃይማኖት በመላው የክርስትና ዓለም ተቀባይነት ያለውን ቅዱስ አትናቴዎስን ፤ በሥላሴ አንድነትና ሦስትነት ጥርጥር እንደነበረው አድርጎ የቢላል ጸሐፊ ማቅረቡ በቅዱስ አትናቴዎስ ጸሎተ ሃይማኖት በ ሚጠቀሙት የክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ሁሉ ታላቅ ትዝብትን ያተርፋል ።

ይልቁንም ይህን በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርቱ ዝነኛ የሆነውን አባት ከነአርዮስ ጋር በማወዳደሩ ጽሑፉ የተምታታና ተጨባጭነት የሌለው ነው ። - - - - የኢየሱስን አምላክነት እንድቀበል ራሴን ባስገደድሁ ቁጥር - - - - ሐሳቤን ለመግለጽ ያልቻልኩ ችሎታ ይቀንስብኛል « የተባለው አነጋገር የቅዱስ አትናቴዎስ ሳይሆን የቢላል የፈጠራ ወሬ ነው ። በጥርጣሬ ማዕበል የዋዠቀውም የደራሲው ወይም የጸሐፊው ሕሊና ነው ።

ቅዱስ አትናቴዎስ በኒቅያ ጉባኤ «ወልድ ፍጡር» ብሎ በድፍረት የተነሣውን አርዮስን ተከራክሮ የረታ ፤ የክርስቶስን አምላክነት ያረጋገጠና የመሰከረ ቀናውንም ሃይማኖት ያስተማረ ፍጹም የቤተ ክርስቲያን አባት ነው ። በሃይማኖተ አበው ከታወቁት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ከፍተኛውን ሰፍራ የያዘና «ሐዋርያዊ» ተብሎ የ ሚጠራ አባት ነው ።

የቢላል ጸሐፊ የቤተክርስቲያን አባቶችን ትምህርት እንደ ሚያውቅ አስመስሎ እነ ኢራንዮስ የክርስቶስን አምላክነት እንደማይቀበሉና ፤ በዚህም ምክንያት እንደተገደሉ አድርጎ ጽፏል ። ለመሆኑ ጸሐፊው ስለ ኢራንዮስ ያውቁ ይሆን ? እስኪ ኢራንዮስ ስለ ክርስቶስ አምላክነት ካስተማረው ትምህርት በጥቂቱ እንመልከት ።

« - - - - ወልድ (ክርስቶስ) ከመጀመሪያ ጀምሮ አብን ገለጠው ምክንያቱም ከመጀመሪያ ጀምሮ ከአብ ጋር ነበርና - - - - እግዚአብሔር ሁሉን ነገር በቃሉ ፈጠረ ፤ ቃሉም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። - - - - አምላክ ሰው ሆኖ አዳነን ። እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። ኢራንዮስ ስለ ክርስቶስ የሚያስተምረው እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ የክርስቶስን አምላክነት በማስተባበሉ እንደተገደለ መናገር ትልቁ ስሕተት ነው ።

አሁንም «ቢላል» የሐሰት አውታሩን በመዘርጋት የክርስትናን ሃይማኖት ለመንቀፍና ለማጥላላት ሲንቀሳቀስ መሣርያ ይሆኑኛል ብሎ ያሰለፋቸው የሐሰት አበጋዞች ፤ «ብርሃኔ ገብረ አረጋይና መሪጌታ መዝገበ ሥላሴ መንግሥቱ ነን» ባዮች ናቸው ።

፩/ ብርሃኔ ገብረ አረጋዊ ነኝ ባይ ፤ በ «ቢላል» ቍ/ ፰ ፲፱፻፹፭ እትም ላይ በደብረ ዓባይ ገዳም ሃያ ዓመታም ሙሉ እንደኖረ ሲያወራ ሐፍረትና ይሉኝታ አልተሰማውም ፤ ካለማፈሩ የተነሣ ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጭ ሳይመነኩስ ፤ ወይም በሕግ ሳይወሰን ቄስ እንደነበረ አስመዘግቧል ።

ቤተ ክርስቲያን የቅስናን ማዕርግ የምትሰጠው «ብርሃኔ ነኝ» ባዩን ለመሰለ ኢ ሕጋዊ ሰው ሳይሆን፤ እግዚአብሔርንና ሰውን ለማገልገል ቃል ለገባ መነኵሴ ፤ በቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት መሠረት በሕጋዊ ጋብቻ ተወስኖ ሰውንና እግዚአብሔርን



www.ethiopianorthodox.org

ለማገልገል ለተዘጋጀ ዲያቆን ብቻ ነው ። «ብርሃኔ ነኝ» ባይ ግን ያለቆብና ያለ ሕጋዊ ጋብቻ በአክሱም ቀስሶ በደብረ ዓባይ ገዳም ለሃያ ዓመታት ያህል አገልጋይ ካህን የነበረ መሆኑን ያወራው አላዋቂነቱንና የሐሰት ስብከቱን ከሚያንጸባርቅ በቀር እውነት አይታይበትም ፤ ይህ ዓይነቱ የሐሰት ንግድም ያከስረዋል እንጂ አያተርፈውም ።

ተጠቃሹ አሁንም ቤተ ክርስቲያን በታቦት ፤ በሥዕልና በመስቀል እንደምታመልክ መዝግቧል ፤ ታቦት ፤ ሥዕልና መስቀል በቤተ ክርስቲያን ይከበራሉ እንጂ አይመለኩም ፤ የሚመለክ አንድ አምላክ ብቻ ነውና ። እሱም «ክፉንና በጎን ለይቶ በማወቅ አዳም. ከእኛ እንዳንዱ ሆነ «በማለት የአካል ሦስት ነቱንና የባሕርይ አንድነቱን ያረጋገጠ (ዘፍ - ፫ - ፳፪) ኋላም አብርሃም ከድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ በሦስት አካላት የተገለጸ ፤ ከሦስቱ አካላት አንዱ በተለየ አካሉ «የዛሬ ዓመት እንደዛሬ ወደ አንተ እመለሳለሁ» በማለት ቃል የገባና ቃሉንም በተግባር ያሳየ ሁሉን ማድረግ የሚችል አንድ አምላክ ነው ። ዘፍ - ፲፰ - ፩—፲፭ ።

፪ - «መሪ ጌታ መዝገበ ሥላሴ መንግሥቱ ነኝ» ባይ በእስልምና ስሙ ኡመር በጎንደር ክፍለ ሀገር ፤ በደብረ ታቦር አውራጃ ፤ ከእስቴ ወረዳ ፤ እስቴ ኢየሱስ በተባለ ደብር በ፲፱፻፵፪ ዓ/ም «ፊታውራሪ መንግሥቱ ኃይሌ» ከሚባሉ አባት መወለዱን በዚሁ «ቢላል» በተባለው ፤ ፪ኛ ዓመት ቍ ፩ ፲፱፻፹፮ ዓ/ም ላይ አስመዝግቧል ።

በተወለደ በ፬ ዓመት ከ፬ ወር ፤ ከ፬ ቀን ፊደል መቁጠሩን ፤ ሠለስት ፤ አርያም ፤ መስተጋብእ ተምሮ ለመሪጌትነት መብቃቱን ሲያወራ አላዋቂነቱን ለማወቅ አልታደለም ።

በጎንደር ክፍለ ሀገር በ ፪ገኝ ደብረ ዓባይ በተባለ ገዳም የአሥራ አራቱን ቅዳሴያት መዝገብ መምህር ወንጌሉ በሀብቱ ከ ፪ባሉ አስተማሪ ተምሮ መመረቁን አውርቷል ። እሱ የፈጠራቸው ሌላ ጎንደርና ሌላ ደብረ ዓባይ ይኖሩ ይሆን ? በጎንደር ደብረ ዓባይ በደብረ ዓባይ መምህር ወንጌሉ የሚባሉ የቅዳሴመምህር የሉም እኮን ! «ኡመር» ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በመመራመር ፲፮ ዓመታትን እንዳሳለፈ ሲያወራ ፤ «በ፲፱፻፷፭ ዓ/ም በአዲስ አበባ የቅድስት ማርያም ዲያቆን ነበርሁ» ብሏል ።

በማኅበረ ሥላሴ «ከጉባኤ ቃና እጣነ ሞገድ ድረስ ተምሬያለሁ» ሲል ምን ማለቱ ይሆን? በቅኔያት ውስጥ ዕጣነ ሞገድ የሚባል የለም ! ! አለመማሩንም የ ፪ገልጠው ይኸው ነው ።

ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፷፭ ዓ/ም በዓለ ጥምቀት እንደነበረ ሲያወራ ሐፍረትና ይሉኝታ አልተሰማውም ! ! ከመቼ ወዲህ ነው በዓለ ጥምቀት ፲፰ ቀን የዋለው ።

በዚሁ በዓለ ጥምቀት ታቦት የተሸከመ ቄስ አልንቀሳቀስ ከማለቱ የተነሣ በተፈጠረው ንትርክ ፓትርያርኩ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስና ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ባደረሱበት ተግሣጽ ተበሳጭቶ ሃይማኖቱን እንደካደና ወደ ትውልድ ሀገሩ እንደ ተመለሰ ፤ ዘመድ አዝማድ ተሰብስቦ «ወድዶ አይደለም እንጂ የተነካበት ነገር ይኖራልና ለማንኛውም ወደ ኢየሩሳሌም ቢሔድና በዚያ ያሉ ዘመዶች ቢያሳክሙት ፤ ይሻላል ተብሎ» ሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ወደ ኢየሩሳሌም መወሰዱን አስመዝግቧል ። (እንደ ቢላል አባባል አሁንም ኡመር የዳነ አይመስልም) ።

ወዲያው ኢየሩሳሌም እንደገባ «ሸኽ ኑር ሱፋሕ» (ኡብዱል ሐኪም ) የተባሉ ፍልስጥኤማዊ በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፈ መጽሐፍ ሰጥተውት ከቤቱ ወስዶ እንዳነበበ ይናገራል ። ምን ዓይነት ስጦታ ቢኖረው ነው ሳይማር የዕብራይስጥን መጽሐፍ አንብቦ የተረዳው? ወዲያው ከሃያ ቀናት በኋላ ነሐሴ ሁለት ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ይህን የዕብራይስጥ መጽሐፍ ይዤ ወደ ሀገሬ ተመለስሁ»ይላል ። እንግዲህ ይህ ዓይነቱ ሰው ነው በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፈ በርናባስ የተባለ ወንጌል ተርጉሞ ፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መሐመድ በኋላ ዘመን መነሣት ትንቢት ተናገረ የሚለን ! ። እንዲህ ዓይነቱ ሰው የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ምሥጢር መርምሬአለሁ የ ፪ለን ! ።

«ኡመር» ያለውን ሁሉ ይረሳና እንደገና የሦስተኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ እንደነበረ በቤተሰብ ችግር ምክንያት ማቋረጡን ሲያወራ አሁን ጨርሶ ዘንግቶ በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም የ፲፩ኛ ክፍል ተማሪ እንደ ነበረና የዕድገት በኅብረት ዘመቻ መዝመቱን በዘመቻ እያለ አንድ ሙስሊም ጓደኛው በሰጠው መጽሔት ምክንያት የእስልምና ሃይማኖት እንደ ተከተለ ሐሳቡን ይደመድማል ።

የቢላል መጽሔት አዘጋጆች ሊያውቁት የ ፪ገባ እውነት ፩ — በእስቴ ወረዳ ፊታውራሪ መንግሥቱ ኃይሉ የሚባሉ የሉም አልነበሩም ።
፪— እስቴ ኢየሱስ ተብሎ የሚጠራ ደብር የለም
፫— በጎንደር ደብረ ዓባይ የ ፪ባል ደብር የለም
፬— በደብረ ዓባይ መምህር ወንጌሉ ሀብቱ የሚባሉ የሉም
፭— በዓለ ጥምቀት ምን ጊዜም በ፲፰ ቀን አይውልም ውሎም አያውቅም ወደፊትም በዚህ ዕለት አይውልም ። ብርሃኔ ገብረ አረጋዊና መዝገበ ሥላሴ መንግሥቱ ነኝ ባዮች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እናዋርዳለን ብለው በቁመታቸው ሙሉ ከ ፪ዋሹ በሌላ ሙያ ጠንክረው ቢሠሩ እንደሚጠቀሙ ቢገነዘቡ መልካም ነው ። የቢላል መጽሔትም በሌላ የእምነትና የነገረ ሃይማኖት ትምህርት ክልል እየገባ የማያውቀውን በመተቸትና የተምታታ አሳብ በማቅረብ በፍቅርና በወንድማማችነት የኖረውን ሕዝብ ወደቁጣ የሚያነሳሳ ጽሑፍ ከመሠንዘር እንዲቆጠብ እንመክራለን ። በምክሩ ሁሉም እንዲተባበርም እንጠይቃለን ።

የመንበረ ፓትርያርኩ የሥነ ጽሑፍ ኮሚቴ ።



# “ከሐሰተኞች መምህራን ተጠበቁ”

ከመምህር ሀብተ ማርያም ተድላ

ሐሰት የእውነት ተቃራኒ እንደሆነ ይታወቃል ፣ ከምን የተገኘ ነው ቢባል ደግሞ ሰፋ ያለ ታሪክ አለውና በማስተዋል መመልከት ይገባል ።

መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ኤልሻዓዳይ (ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ) ሰይማይንና ምድርን ፣ በውስጣቸውም የሚገኘውን የሚታይና የማይታየውን የ ፪ንቀሳቀስና የማይንቀሳቀ ሰውን ፍጥረት ሁሉ በቃል ብቻ ለይኩን ብሎ ከፈጠረ በኋላ በመጨረሻ ሰውን በአርአያውና በአምሳሉ ፈጠረ ።

ሰውን ሲፈጥረው እንደ ሌሎች ፍጥረታት በቃል ብቻ ይሁን በማለት ሳይሆን ከምድር አፈር ወስዶ አሳምሮ ፈጥሮታል ። በአፍንጫውም እፍ ብሎ የሕይወት እስትንፋስን አሳድሮበታል ። ስለዚህ የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት ተለይቶ አዋቂና ተመራማሪ ሆነ ፣ ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፳፮ ፡ ፳፱ ፤ ፪—፯ ።

ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ ሰውን አክብሮና የፍጥረታት ሁሉ ገዥ አድርጎ ረኀብ ችግር ከማይገኝባት ፣ በአበባና ፍሬ በተዋበች ገነት አኖረው ። በዚህ ጊዜ የብርሃን መላእክት እየመጡ ይገብሩት ነበር ። ፍጥረታት ሁሉ ይገዙለት ነበር ። ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፲፱—፳፩ ።

ልዑል እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው እንደ መላእክት በሕገ ልቡና ፈጣሪውን እያመሰገነ እንዲኖር እንጂ መጽሐፋዊ ሕግ አልነበረውም ፣ በፈጣሪና በፍጡር መካከል ግን ሕገ ልቡናዊ እንዲኖር አስፈላጊ በመሆኑ በገነት ያለውን ሁሉ ትበላለህ ፣ በገነት መካከል ያለችውን ፤ ከፉንና በጎን ለይታ ከምታስታውቀው ዛፍ ፍሬ ግን እንዳትበላ ፣ ከእሷ በበላህ ጊዜ ሞትን ትሞታለህ የሚል ትእዛዛዊ ሕግ ሠራለት። የአዳምን ክብር የተመለከተ ክፉ መንፈስ ባደረበት ቅንዓት በሐሰት ከዚህች ዛፍ ፍሬ በበላችሁ ጊዜ ዓይናቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም እንድትሆኑ ስለሚያውቅ ነው እንጂ ሞትን አትሞቱም አላቸው ።

አዳምና ሔዋን የሐሰት መምህራቸው የዲያብሎስን ምክር ሰምተው የእግዚአብሔርን ሕግ ጣሱ ፤ ትእዛዙን አፈረሱ ፤ ከፈጣሪያቸው ጋር ተጣሉ ፤ የሐሰት መምህራቸውም በሕይወት ይኖሩ የነበሩትን የሞት ሞት አስፈረደባቸው ፤ ምድረ ፋይድም (የፍዳ ዓለም) እንዲወርዱ አደረጋቸው ፤ ጥረው ግረው ፣ ወጥተው ወርደው ፣ በላባቸው ባገኙት ፍሬ እንዲኖሩ አስፈረደባቸው ። ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፩—፳፬ ፤ ሔኖክ ፲፱ ፣ ፳፪ ።

የሐሰት ምንጭዋ ፣ መገኛዋ ዲያብሎስ መሆኑን ከተረዳን ዘንድ ፡— በየጊዜው ፣ በየዓረፍተ ዘመኑ የ ፪ነሡት የሐሰት መምህራን የዲያብሎስ መልእክተኞች መሆናቸውን ማወቅና መጠንቀቅ የእያንዳንችን ድርሻ ይሆናል ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “ከሐሰቶች መምህራን ተጠበቁ” በማለት ሲያስጠንቅቅ ፡ ሐሰተኛ የሐሰት አባት ዲያብሎስ መሆኑንም አስተምሮአል ። ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፭ ፤ ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፵፪—፵፰ ።

ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በ፭፻፹፯ ዓመት አካባቢ እሥራኤል ተማርከው ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን ተወስደው በነበሩት ጊዜ ሐናንያ የ ፪ባል የሐሰት ነቢይ ተነሥቶ ነበር ። በሐሰተኞች ነቢያት ዘንድ ሐፍረትና ይሉኝታ የለምና እግዚአብሔር ሳይልከው እንደላከው አስመስሎ “ናቡከደነጾር ወደ ባቢሎን የወሰደው የቤተ መቅደስ ዕቃ ሁሉ በሁለት ዓመት ውስጥ ወደ ኢየሩሳሌም ይመለሳል ፤ ኢኮንያንንና የይሁዳን ምርኮ ሁሉ ወደዚሁ ሥፍራ እመልሳለሁ፤ የባቢሎንን ንጉሥ ቀንበር እሰብራለሁ ? ይላል እግዚአብሔር” በማለት የሐሰት ትንቢት ተናገረ ፤ በእውነተኛው ነቢይ ኤርምያስ አንገት ላይ የነበረ



www.ethiopianorthodox.org

ውን ቀንበር ወስዶም በሕዝቡ ፊት ሰበረ ። ኤር ፣ ፳፰ ፣ ፩—፲፪ ።

በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ ኤርምያስ መጣ ፤ "ለሐናንያ እንዲህ ብለህ ንገረው፤ አንተ የሰበርኸው የዕንጨት ቀንበር ነው ፤ እኔ ግን የብረት ቀንበር እሠራለሁ"

ኤርምያስ ይህን የእግዚአብሔር ቃል ሰምቶ ለሐናንያ እንዲህ አለው ፤ ሐናንያ ሆይ ፣ ስማ ፤ ይህ ሕዝብ በሐሰት እንዲታመን አድርገሃል ፣ እግዚአብሔር አልላከህም ፣ ስለዚህ በእግዚአብሔር ላይ ዓምፀሃልና በዚህ ዓመት ትሞታለህ ፤ -----እስራኤልም በባርነት ገና ሰባ ዓመት በባቢሎን ይኖራሉ ። - - " ብሎ የእግዚአብሔርን መልእክት ነገረው ። የእግዚአብሔር ቃል የማይታበል በመሆኑም ፤ ኤርምያስ እንዳለው ሐናንያ በዚያው ዓመት ሞተ ። ኤር ፳፰ ፣ ፲፫—፲፯ ።

አሁንም በነቢዩ በኤርምያስ ያደረው የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲህ አለ ፣"በመካከላችሁ ነቢያቶቻችሁና ሟርተኞቻችሁ አያታልሏችሁ ፤ ሕልሚዎቻችሁም አያስቷችሁ ፤ በስሜ ሐሰተኛ ትንቢት ይነግሩአችኋል ። እኔ አልላክኋቸውም ፤ ኤር ፳፱ ፣ ፩-፲፩ ።

የሐሰተኛው ነቢይ የሐናንያ ትንቢት ከንቱ ሆነ፤ በእውነተኛው ነቢይ በኤርምያስ ትንቢት መሠረት፤ እስራኤል በባቢሎን ሰባ ዘመን በባርነት ከኖሩ በኋላ በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ ዘመነ መንግሥት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ። ዕዝ ፩ ፣ ፩—፲፩ ፤ ዜና መ ፣ ካልዕ ፴፮ ፣ ፳፪ ፣ ፳፫ ፣ ኢሳ ፣ ፵፬ ፣ ፳፰ ።

እንደዚሁም ሸማያ የሚባል ሌላ የሐሰት ነቢይ ተነሣ ፤ የእውነተኛውን የኤርምያስን ትንቢት በመቃወም በምርኮ በባቢሎን ለሚገኙት እስራኤላውያን ደብዳቤ ጻፈ ። በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ" እግዚአብሔር ስለ ነሐማዊው ስለሸማያ እንዲህ ይላል ብለህ ወደ ምርኮኞቹ ሁሉ ላክ ፤ እኔ ሳልልከው ሸማያ ትንቢት ተናግሮላችኋልና ፤ በሐሰትም እንድታምኑ አድርጓችኋልና ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ነሐማዊውን ሸማያንና ዘሩን እቀጣለሁ ፤ እኔም የማደርግላችሁን መልካሙን ነገር የ ሚያይ ሰው በመካከላችሁ አይኖርላቸውም" ።

የሐሰተኛ ነቢይ ፍጻሜ ታይቶ መጥፋት ነውና ሸማያ ከእነዘር ማንዘሩ ጠፋ ፣ ተመደሰሰ ። ኤር ፣ ፳፱ ፣ ፴—፴፪ ።

አሁንም በዘመናችን ብዙ ነቢያተ ሐሰት እንደሚነሡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ አስተምሮናል ፣ አስጠንቅቆናልም ።" ብዙዎች ሐሰተኞች መምህራን ይመጣሉ ፤ ብዙዎችንም ያስቷቸ ፤ ከዓመፅና ከክፋት የተነሣም ፍቅር ከብዙዎች ትጠፋለች" ማቴ ፣ ፳፬ ፣ ፲—፲፫ ፣ በማለት የሰጠው ማስጠንቀቂያ በየጊዜው ሲፈጸምና በተግባር ሲተረጎም እያየን ነው ።

"እኔ ክርስቶስን እንመደሰልሁት እናንተም እኔን ምሰሉ" ያለን ፣ ጌታውን የመሰለ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ፣—" እኔ ከሔድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ነጣቂዎች ተኩላዎች እንደ ሚነሡ አውቃለሁና ፤ ከእናንተ መካከል ሰዎችን ወደ እነሱ ይመልሱ ዘንድ ጠማማ ትምህርትን የ ሚያስተምሩ ሰዎች ይነሣሉ የሐ ፣ ሥ ፣ ፳ ፣ ፳፭—፴፩ ፤ ፩ኛ ፣ ቆሮ ፣ ፲፩ ፣ ፩ ። ጺድቃን ፣ ይመስላሉ ፤ የጽድቅን ኃይል ግን ይክዱታል ፤ እንደ እነዚህ ያሉትን ራቃቸው። ፩ኛ ፣ ጢሞ ፣ ፫ ፣ ፩—፮ ፤ የሚተናኮሉ የክርስቶስን ሐዋርያት መስለው ዓመፅን የሚያደርጉ ሰዎች አሉ፣ ይሁም አያስደንቅም ፤ ራሱ ሰይጣን እንደ ብርሃን መልአክ ይመስላልና - - - - ፪ኛ ቆሮ ፣ ፲፩ ፣ ፲፫—፲፬።

ሐዋርየው ፍቁረ እግዚእ ዮሐንስም "ወንድሞቻችን ሆይ ! ! መንፈስን ሁሉ አትመኑ ፤ ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት ወደዚህ ዓለም መጥተዋልና ፤ እነዚህ ነቢያት የእግዚአብሔርሔር መሆን አለመሆናቸውን መርምሩ " ይላል ፩ኛ ፣ ዮሐ ፣ ፬ ፣ ፩ ።

በጊዜያችን መንፈሳውያን ሳይሆኑ መስለው የሚታዩ የሐሰት ነቢያት (ባሕታውያን ነን ባዮች) እውነተኛውን ክርስቲያን ግራ ሲያጋቡ ይገኛሉ ።

ቤተ ክርስቲያኒቱን የሌባ ዋሻ አድርገው ሊጠቀሙባት ሲሞክሩ ክርስቲያን ይህን እየተመለከተ በአርምሞ ሊመለከተው ይገባል ? የእነሱ ሕልም እስኪተረጎም ድረስ ነውን ? ሐላ ፊዎቻችሁ አያስቷችሁ ተብሏልና ፣ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ቤተ ክርስቲያኑንና ሃይማኖቱን በትጋት ይጠብቅ ፤



# የ ገ ና ት ዝ ታ

ኢትዮጵያ የገናን በዓል ከሚያከብሩት ጥንታዊያን አገሮች አንዷ ናት ። ከሰሜን እስከ ደቡብ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ የሚገኙት ቤሔረ ሰቦች በልዩ ልዩ ቋንቋዎችና ባሕሎች የገና በዓልን ያከብሩታል ።

የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሃይማኖት በዓላትን ማክበር የጀመሩበት ዘመን በብሉያትና በሐዲሳት መጻሕፍት የታወቁ ቢሆንም በዓመት ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ከ ሚከበሩት ዐበይት በዓላት አንዱ የገና በዓል ነው።ሲ ታውንቱም ጌና «በዓለ ልደት ብሂል» ብለውታል ። የገና በዓል ሁለት ዘይቤዎች አሉት አንደኛው ዘይቤ ገና ልደተ ክርስቶስ ማለት ሲሆን ሁለተኛው ገና በትንቢት ወደፊት የሚፈጸም ወይም የሚገለጥ ክብር መኖሩን ያስረዳል ። ምን አልባትም ጥምቀትን ሳይሆን አይቀርም ።

የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ የገናን በዐል እንደየችሎታው በማሰናዳት በዓሉን የማያከብር የለም ። የገና በዓል የክርስቶስ ልደት በመሆኑ ክርስቲያኖች ሁሉ በናፍቆት የሚጠብቁት ዓመታዊ በዓል ነው ። ይህንን ክቡረ በዓል በስሜትና በፈቃደኝነት የልዩ ልዩ እምነት ተከታዮችም ከወንድሞቻቸው ከክርስቲያኖች ሳይለዩ የሚያከብሩ አሉ ።

የገና በዓል በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በዓለም ታሪክ የተጀመረው በቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት በተለይም በደገኛዪቱ በእሌኒ ንግሥት የበላይ ጠባቂነት ከ፫፻፳፭ ዓ/ም ጀምሮ የክርስትናን እምነት በተቀበሉ አገሮች ሁሉ ሲከበር እንደቆየ ይታወቃል።

የገናን በዓል የምዕራብና የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናትም በተለያዩ ቀናች በቅዳሴ ያከብሩታል።

የገና በዓል ልደተ ክርስቶስ በምሥራቃውያንና በምዕራባውያን ሕዝቦች በአክብሮትና በናፍቆት የሚከበር በዓል በመሆኑ ልዩ ልዩ ጌጣ ጌጦችን በመሥራት በየዓመቱ ይጠብቁታል ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፣ የገናን በዓል በጸሎት በማሕሌትና በቅዳሴ ታከብራለች ። በቤተ መንግሥቱም በኩል በዐሉን ለማብሠር መድፍ እየተተኮሰ ሲከበር ኖሮአል ። በቤተ መንግሥቱና በቤተ ክህነቱም ስለ በዓሉ ክብር ዐቢይ ግብር ሲበላ ቆይተዋል ። የቤተ መንግሥቱ ግብር እስከ ምጽአተ ደርግ ዋዜማ መፈጸሙ ይታወሳል ።

የገና በዓል በኢትዮጵያ በገጠርና በከተማ በሀብታምና በደሃ ቤት እኩል ደረጃ ተሰጥቶት በመከበር ላይ የ ሚገኝ በዓል ነው ። ይህ በዓል በገና ጨዋታና በፈረስ ጉግሥ ታላቅ የባሕልና የስፓርት ጨዋታ የሚታይበት ቀንነው።ሕፃናት እንደ ሕፃንነታቸውጎልማሶችም እንደ ጉልማስናቸው ማንኛውም ሰው እንደ አድሜውና እንደ ማዕረጉ ስለ በዓሉ ክብር እርአያና ምሳሌ እየሆኑ በልዩ ባህላዊ ጭውውት ያሳልፉታል።

በአገራችን የገና በዓል ከፍተኛ በዓል በመሆኑ ማንም ሰው ለንግድ ቢወጣ ወይም ለሥራ ከቤቱ ወጥቶ ቢሰነብት የገናን በዓል በቤቱ ለማክበር ከሄደበት ለመመለስ ብርቱ ጥረት ያደርጋል ። በተለያዩ አገሮችና አካባቢዎች የሚኖሩ ወገኖችም ወደተወለዱባቸው መንደሮች የሚመለሱት ለገናና ለጥምቀት በዐል ነው ።

የገና በዓል በኢትዮጵያ ማኅበራዊና ብሔራዊ በዓል ሁኖ በመኖሩ የማንኛውም እምነት ተከታዮች ከክርስቲያን ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ጋር ይገባበዙበታል ። ስጦታ ይሰጣጡበታል ማሕበራዊ ጨዋታዎች ይጫዋወቱበታል ።

በኢትዮጵያ የገና በዓል አከባበር በጥንግ ፣ በሩርና በፈረስ ጉግስ ጨዋታዎች ይደምቃል ጥንጉም ሆነ የሩር መምቻ ዱላው የሚዘጋጀው ቀደም ሲል ታስቦበት ነው ። ዱላውም ከማንኛውም የዘወትር ዱላ የተለየ ነው ። የእጅ መያዣው ቀጥ ያለ የሩር መምቻው ወገን ቆልማማ (ቆላፋ) ነው ። ከጠንካራ እንጨት የ ሚቆረጥ ፣ በእሳት ተለብልቦ የሚሸለመለምና ጠንካራ ነው ።

ሩሮቹም ጠንካራ የእንጨት ሥር (ቋር) ወይም ከጅማትና ከጠፍር ተሰርተው የ ሚቀርቡ ናቸው ። እነዚህ ሁሉ በአባቶቻችን አገላለጥና አባባል ምሳሌና ዘይቤዎች አሉዋቸው ።

የሩርና የጥንግ ጨዋታ የሚፈጸመው በሰፊ ሜዳ ላይ ነው ። ይህ ሜዳ በሽማግሎች በጫማ ተመትሮ እኩል ከተከፈለ በኋላ በማእከለ ምድሩ ላይ ትንሽ ጉድጓድ ይማሳል ። የግራቀኙ ተጨዋቾች በተገኙበት ሩሩ ወይም ጥንጉ ከጉድጓድ ይገባል በመቆራቆስ ጨዋታው ከጉድጓድ ላይ ይጀመራል ። ተቆራቋሾችም ለየቡድናቸው (ለየጎራቸው) ሩሩን ይመታሉ በዚህ ጊዜ እግር ቢሰበር ራስ ቢተረተር ከጨዋታ ባሕርይ ከሚፈጠር ጊዜያዊ ግጭትና አምባጓሮ በቀር ክስና ውቅስ ካሣና ጉሜ አልነበረም ።

በጨዋታው ወቅት መሸነፍና ማሸነፍ ያለ በመሆኑ በሆታ በመመሰጋገንና በመነቃቀፍ አሸናፊው ወገን ተሸናፊውን እንደዚህ እያለ ሆ ይልበታል«ምን ያለ ነው ይኸ ምን ያለ ነው ሲቃጡት ዝም ያለ ሲመቱትም ያው ነው ይለዋል ።

እምና የገናለት የበላው ሽልጦ ፣ ዛሬም ይታየኛል ከድዱ ተሸጦ ።



www.ethiopianorthodox.org

በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታቸበግለት መተራረብ ያለ ነው ።

በጥንት ጊዜ በረሐ ወርደው ዝሆን ጉሽና አንበሳ አድነው በጦርና በጋሻ ተከላክለው ገድው የተመለሱ ጉተናቸውን ወይም ጉፈሪያቸውን እሳድገው ይቀቡ ስለነበረ በገና ጨዋታ ጊዜ ከተሸነፉ እንደሚከተለው ይገጠምባቸዋል ።

«የገደለበትን አናውቀውም እኛ ሲቀባ ይኖራል እንዳዳል መሚኛ» በተራ ው አሸንፎ የገደሉበትን የት አባከ አውቀኸው እንኳን በረሐውን ሜዳውን አትዘልቀው» ብሎ ይመልስለታል ።

በዚሁ ትርምስምስ ጨዋታ ጊዜ እግሩን የሚሰበር ራሱን የ ሚፈነከት ብዙ ነው ። ይሁን እንጂ ጨዋታውን ማሳደድና ግብ ለማግባት ከመርጥ በስተቀር በቴም በቀል መበቃቀል ወይም መፈላለግ የለም ። ጨዋታው መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ሥርዓት ያለበት ገድል በመሆኑ ነው ። የበዐሉ መንፈሳዊነት ፤ ባህላዊነትና ማኅበራዊነት በሴቶችና ወንዶች ወጣቶች ባህላዊ ጭውውት የተለመደና ያሸበረቀ በመሆኑ ታውቆ ይኖርአል ።

መጋቢ ጥበብ የማነ ብርሃን ተሾመ

---

# የግሸን እመቤት

ገደላ ገደሉ በውበት ተጠምቆ
ጋራው ሸንተረሩ ተነባብሮ መጥቆ ፣
በየማዕዘኑ ሳይጉረብጥ ወርዶ
ኸርው ካለው ገደል ፣ ወጥቶ ሰማይ ንዶ ፣
ሣሩ ሰንበሴጡ በአረንጓዴው ልባስ በጨዛ ጠልወዝቶ
በትናንሽ ብርሃን በወስከምባይ ሙራ
ተሸሞንሙና ፈክቶ
በአዕዋፍ ዜማ ፣ በአበቦች ሽታ
በጦስኝ መዓዛ በከሴ ሽውታ ፣
ቁንጅና ተምጣ ፣ ዕለቱን ተወልዳ
በውበት ተኩላ ከፀሐይ ተዛምዳ ፣
ደምቃ እንደጨረቃ
በተድላ ተሞልታ በሐሴት ፈንድቃ ፣
ከምሁራን አምባ ከሊቃውንት መካን (ቦታ)
ከላይ ከአፋፍ ወጥታ ፣ ከመስቀሉ ዕምብርት
አለች እመቤቴ ፣ ቅድስት ወብፅዕት ፣
የግሸን እመቤት የብርሃን ሠፈር
ነፍሴ ተፍነከንካ ፣ አብቅላ አከናፍ ፤
ከአፀድሽ ገበታ ከደሽ ሳመች
ከብለል ዘለል ብላ ሰላም ለኪ አለች ፤
አንች የግሸን አምባ ፣ አንች ቅርፀ መስቀል
የጌታችን ወዙ ፣ ግማደ መስቀል
የክርስቶስ ደሙ ፣ ግማደ መስቀል
ከለሜዳው ንውድ ፣ ግማደ መስቀል ፣
በክብር ያረፈብሽ መስቀል የርሱ አካል
ወዮ ! ያንቺ መመረጥ ፣ ግሩም መታደል
የመስቀል ምድር ሆንሽ ተቀበልሽ መስቀል ፣
ከእግዚአብሔር አብ ደብር ፣ ከተመሳቀለው
ያው ሠለስቱ መስቀል በገሐድ አየነው ፣
እንዘ ሠለስቱ አሐዱ ፣ ወእንዘ አሐዱ ሠለስቱ
አይደል ተዋሕዶ ፣ ከጥንት ከጥዋቱ ፤
ግሸን ደብረ ከርቤ ቅድስትዋ ምድር
ምንኛ ያስገርም ፣ መስቀል ንብርብር ፣
ሦስት ሆኖ አንድነት በብርሃን ሲናኝ
ኃጥአንን ሲፈውስ ፣ ሲደግፍ አማኝ ፣
የግሸን እመቤት ፣ የብርሃን አለላ
ፍቅርን በዕቅፍዋ ፣ ምህረት በጉንዋ አዝላ
ቅድስተ ቅዱሳን ፣ ስብሕት ወቡርክት
ድንግል የኛ እመቤት ፣ ጽዮን የኛ እናት ፣
ከከዋክብት ልቃ ከፀሐይም ደምቃ
ከተለያየን ወንዝ ርቃ ፣ ወጥታ መጥቃ ፣
ከበሽሎ ጅረት ፣ ከዲልባ ጊዮርጊስ
ከወዲህ ባሻገር ከዓሸን መቅደስ ፣
ከተአምራት ደብር ከመስቀሉ ሀገር
ተሰማ አዲስ ዜማ ፣ በመላእክት ምስጢር ፣
ድንግል የመሥረፅዋ በብርሃን ሰማይ
ጽድቅን የማዝነብዋ ከዓይኖችዋ ማይ ፣
ምዕመናን ጉረፉ ከባሌ ከአዋሳ ፣
ከቾሟራት ፣ ከመንዝ ከዋድላ ፣ ከቀርሳ ፣
ጠበልሽን ሊጠጡ አፈርሽን ሊያስሱ
ቆንጥረው በእራፊ በረከት ሊወርሱ ፣
ግሕሴት ዘነበ ፣ ወረብ አየር መላ
ትሩፋት ተቀዳ የቅድስት ወለላ ፣
በሰዎች ልቦና ፍቅር ዓርጎ ወረደ
ኃጢአትን ሠርስሮ መንግሎ እየናደ ፣
ሜጨት የእናት ሙቀት አጥብቃ ትሻለች
እምቦሳ በእናትዋ መላስ ትወዳለች
ከእናት ቡግ ግልገልዋ መጥባት ታፈቅራለች
የግሸን እመቤት ነፍሴ ትከንፋለች
ከዙፋንሽ ብርሃን ትንፈራፈራለች
በፍሥሐ ወሐሴት እጅግ እየራደች
ከፀጋሽ በረከት ጠምቷት ትርሳለች ፣
በኃጢአት ነድዳ ፣ አርራ ከስል ብላ
የርህራሔሽን ጠል ትሻለች እምርራ ፣
ግሸን እመቤቴ የእሸት ፍልቅቅ
ከዕንቊ የጠራሽ የሰማያት ወርቅ ፣
ቅድስተ ቅዱሳን ክብርት ወልዕልት
የመንግሥተ ሰማይ ማከዳ ንግሥት ፣
ከጠሩ የጠራች ንጽሕት እምንጹሐን
የማትጠፊ ፋና የርህራሔ ድንኳን ።

ቀሲስ ዳኛቸው ካሣሁን



# መልካም ምሳሌነት

«ለሁሉም ጊዜ አለው ።» የሚለው ጥቅስ በስነ ፍጥረት ዓለም በግብር ሲታይ የሚኖር ታላቅ የፍልስፍና ቃል ነው ።

ለሳቅ ፤ ለደስታ ጊዜ እንዳለ ሁሉ ለኀዘንና ለልቅሶም ጊዜ አለ ። እነዚህ በሰው ሕይወት ውስጥ የሚመላለሱ የመከፋትና የመደሰት ወቅቶች በተራራቀ ጊዜ እንኳ ሳይሆን በቀን ውስጥ ተለዋውጠው ሊደርሱ የሚችሉ ናቸው ። ሰዎች ኀዘንና ደስታ መኖራቸውን ቢያውቁም ፤ ኀዘኑ በምንና መች ? እንደሚደርስ ፤ ደስታው በምንና እንዴት ? እንደሚገኝ አያውቁም ። ለኀዘን ምክንያት የሚሆን ችግርን በመጠንቀቅ ማምለጥ ፤ ለደስታ ምንጭ የሚሆኑ ነገሮችን በመጨነቅ ማግኘት አስቸጋሪ ነው ።

በዚያም ሆነ በዚህ ኀዘንና ደስታ በጪትና ማታ ፈረቃ በሰው ሕይወት ውስጥ የሚመላለሱ ስለሆነ ያዘኑ የሚደሰቱበት ፤ ደስ ያላቸው ደግሞ የ ሚያዝኑበት ጊዜ አይቀሬ ነው ።

ውስጣዊ ስሜትን ፈንቅሎ ወደ ዕንባ መፍሰስ የሚያደርስ ትልቁ የኀዘን(የመከፋት) መግለጫ ልቅሶ ነው የልቅሶው መንስኤዎች ብዙ ናቸው ። የሚያስለቅሱ ነገሮችም ሞልተዋል። መለያየት ያስለቅሳል፤ ናፍቆት ያስለቅሳል ፤ ረሀብ ፤ ማጣት መቸገር - - - ያስለቅሳል ፤ ንዴት ያስለቅሳል ፤ በሽታ ያስለቅሳል ደስታና ፍቅርም የሚያስለቅሱበት ፤ እስከሞት አደጋም የሚያደርሱበት ጊዜ ይኖራል ።

የማስለቀስ ጠባይ ባላቸው ነገሮች የማይነኀበኝና የማያለቅስ ሰው ይኖራል ለማለት ባይቻልም፤ ሁሉን ሰው ያስለቅሳል ተብሎ የ ሚገመተው ሞት እንኳ የማያስለቅሳቸው ሞልተዋል ። በተለያየ ልምድና አመለካከት ስለማያዩት ነው ። በኛ ሀገር በአብዛኛው በሰው ኅሊና ትልቅ ኀዘን የሚጥለው የ ሚያስለቅስ ሰው ሞት ነው ። ዛሬ ዛሬ የመሻሻል ምልክት ፤ እየታየ ቢመስልም ቀደም ባሉት ጊዜያት ፊትን መንጨት ፤ ደረትን መድቃት ፤ አካልን በእሾህና በስለታም ነገሮች እያቆሳሰሉ ጠባሳ ማውጣት ፤ ማቅና አዳፋ ልብስ መልበስ ፤ ወገብን በጠፍርና በገመድ ማሠር፤ጦም ውሎ ጦም ማደር ፤ እየተንሰቀሰቁ ማልቀስና በዕንባ ዐይኖችን ለጉዳት ማጋለጥ ወዘተ - - - የተለመደ ባህል ሆኖ ቆይቷል ። ግጥም እየደረደሩና የሙታን ወገኖችን ስም እያነሳሱ የማስለቀስን ሙያ የተካኑ አልቃሾችን አስለቃሾችን በገንዘብ እያቀጠሩ ማውረድም እስከ ቅርብ ጊዜ የ «ከማን አንሼ» ልምድና ፈሊጥ ሆኖ ቆይቷል ። አሁንም አልፎ አልፎ ይደረጋል ። የአስለቃሾች የእንጉርጉሮ ዜማ ፤ የጥሩምባ ድምፅና ምሥጢር ከዕድሜ ፤ ከሴትና ወንድ የሚያ መታዎች ፤ ከሰብአዊ ቅርጾችና አቋሞች አንጻር የ ሚነሡት ነጥቦች የሰው ዘመን ጥላነትና የአዱኛ ብላሽነት ሲመዘንባቸው የሞተበትን ብቻ ሳይሆን ለኀዘን ተካፋይነት ጉራ የሚለውንም ሁሉ ጨምሮ ያስነባል ። ለጥቂት ሰዓትም ቢሆን የምድራዊን ሕይወትና ኑሮን ከንቱነት አስገንዝቦ ያስተምራል ። የማልቀስ ባህልና ልምድ ያላቸው ወገኖችም «ጥሩ ልምድ ነው» ኀዘንን ያወጣል ይሉታል ።

በኛ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ይህ ሁሉ አይደገፍም ። የዚህም ምክንያቱ በመሠረቱ አንድ የቤተሰብ አባል በተፈጥሮ ግዴታ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ በኀዘንና በልቅሶ የማይመለስ ፤ ልቅሶው ሟችን በምንም መልኩ የማይጠቅም ከመሆኑም ሌላ ፣ በቀረው ወገን ሕይወትና ጤንነት ላይ ልቅሶ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ ስለሆነ ነው ። በክርስትናው እምነትም ሰው ቢሞትም በመቃብር አፈር ተበልቶ አይቀርም ይነሳል ፤ ለዘለዓለምም በሕያውነት ይኖራል ።

በዚህ ትምህርትና እምነት የሚኖር ክርስቲያን ለሞተ ወገኑ መሪር ኀዘን ማዘንና የቀቢጸ ተስፋ ልቅሶ ማልቀስ በትንሣኤ ተስፋ እንደማያምን ያስቆጥረዋል ስለሆነም አብሮ የኖረ ሰው ለዘለዓለም ከዚህ ዓለም ሲለይ ነፍሱ ከሥጋው ስትለይ ፤ አስከሬኑ ከቤት ሲወጣ ፣ ወደመካነ ዕረፍት ሲገባ ብቻ «ሰው ሆይ ! መሬት ነህና ወደ መሬትነትህ ትመለሳለህ» የተባለውን በማሰብ ዕንባን አፍስሶ መሰናበት እንደሚገባ ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች። ፊትን መንጨት ጸጉርን መላጨት ፤ ማቅ መልበስ ፣ ጥቁር ጨርቅ ሁሉ የተከለከለ ነው ።

ይህን መግለጫ በማስቀደም ልናስተላልፈው የፈለግነው መልእክት ከጉራጌው ኅብረተሰብ ያገኘነውን የኀዘን ማሻሻያ ትምህርትና ኑዛዜ ነው ።

## ኑ ዛ ዜ ፤

እኔ ወሮ/ - - - - - እና ባለቤቴ አቶ - - - - - - - በሕግ ተጋብተን - - - - - - - ልጆች አፍርተናል ። ከልጆቻችን መካከል በሞት የተለዩም ሲኖሩ ከፊሎቹ ተባርከውልን በጥሩ ሁኔታ አሳድገን ድረን ኩለን ለጋብቻ ለቁም ነገር አብቅተናል ። ያደጉትና ቤት ንብረት ያቋቋሙትም ልጆቻችን እኛ ወላጆቻ



www.ethiopianorthodox.org

ቻው በሸመገልንበት ጊዜ በተራቸው እየታዘዙ ጦረውናል ። እናትም አባትም ሳንለያይ አገልግለውናል ። ስለዚህም መርቀናቸዋል ለሕይወታችን የሚያስፈልገውን ሁሉ በማቅረብ እንዳይርበን ፤ እንዳይጠማንና እንዳይበርደን አድርገው ተከባክበውናል ። እንዳበሉን ይብሉ ፤ እንዳለበሱን ይልበሱ ፤ የሚሰጡት አያሳጣቸው ። አንድ እጃቸው በጋ ፤ አንድ እጃቸው ክረምት ይሁን ። የወለዱአቸው ይባረኩ ። ልጆቻችን በሙሉ እኛ የበላነውን ይብሉ ፤ የኛን ዕድሜ ያግኙ ፤ ምርቃታችንን በምድር አያስቀርባቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ይድረስ ልጆቻችን ታላላቆቹንም ታናናሾችንም ልጆቹንና ያልጆቹን ልጆች አቅርቡአቸው ፤ አታርቋቸው ። ፍቅር ይኑራችሁ።ሳያስቀይሙና ሳይቀየሙ የረዱን ልጆቻችን ሁሉ ብድር ይግባቸው ። እግዚአብሔር የተባረኩና የተመረቁ ጢሪ ልጆች ይዘዝላቸው ። የልጆችን ሃይማኖትና ጠባይ ይዘው ይደጉላቸው ። በሕይወታችን እያለን በሸመገልንበትና ረዳት በፈለግንበት ጊዜ በሚገባ የረዳችሁን ስለሆነ ልቅሶ የለም ። የኀዘን ምልክት ጥቁር ልብስ እንዳትለብሱ በማርያምና በልጅዋ በመድኃኔ ዓለም ስም ከልክለናል የምስጋናችን ዕለት ነጭ ኩታ ልበሱ ራሳችሁን ቅቤ ተቀብታችሁ ኀዘናችሁን አብርዱ ።

ከነ አቶ ዘለቀ ዋኬኔ ቤተሰብ

መልካም ኑዛዜ ፤ ምርቃት ፤ በረከት ፤ ትምህርት ያለበት ስለሆነ ሁሉ ቢከተለው መልካም ነው ።

ከቀሲስ ዳኛቸው ካሣሁን

---

# ጨዋታና ቁም ነገር

ከቀሲስ ዳኛቸው ካሣሁን

ጥበብን ለምን ትፈልጓታላችሁ? ከገበያ አትገዛ፣ ከምድር አትበቅል ከኪሩቤል ጀርባ ካለው ከሕይወት ምንጭ ቅዱ ። (መጽሐፈ ጨዋታ)

በእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብናኃይል ፤ ማስተዋልም አለ ፤ ኃይልና ጥበብ በርሱ ዘንድ ናቸው ። (ኢዮ - ፲፪ ፡ ፲፫)

ቅቤ ለመጽሐፍ ዘመዱ አይደለም ፤ መጽሐፍ ግን ለሰው ቅቤ ነው ፤ (መጽ - ጨዋታ)

የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ፣ ልብንም ለማቅናት ፤ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል ። (፪ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፮) ።

ተከል ሆኖ ካላፈራ ፤ ሰው ሁኖ እግዚአብሔርን ካልፈራ መቅረጥ አይቀርለትም ። (መጽ ፡ ጨዋታ)



www.ethiopianorthodox.org